# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 070 ኅዳር 10 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## ‹‹ በመንግሥት የፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ የታየው አመርቂ ውጤት በግሉ ዘርፍም እየተደገመ ነው ››

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በመንግሥት የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ የታየው አመርቂ ውጤት በግሉ ዘርፍም እየተደገመ መሆኑን የሚያሳዩ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአቃቂ ቃሊቲ በተለያዩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ያደረጉትን ጉብኝት አስ መልክቶ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው በሰጡት ማብራሪያ እንዳሉት፤ ባለፉት ዓመታት ፕሮጀክቶችን በፍጥነትና በጥራት ሰርቶ በማጠናቀቅ አመርቂ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ ይህ ልምድ ከመንግሥት ፕሮጀክቶች አልፎ በግል ዘርፉም ከፍ ያለ ሥራ በመሥራት፣ በጥራትና በፍጥነት ሥራዎችን በማጠናቀቅ እየተደገመ ነው፡፡

‹‹በመንግሥት የፕሮጀክት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ‹‹ በመዲናዋ እየተከናወነ ያለው የከተማ ግብርና ለሌሎችም ከተሞች ተምሳሌት የሚሆን ነው ››

- ፀጋ ለማ(ዶ/ር)
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእንስሳት ልማትና ልህቀት ማዕከል ኃላፊ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ እየተከናወነ ያለው የከተማ ግብር ሥራ ለሌሎችም ከተሞች ተምሳሌት የሚሆን መሆኑን የከተማ አስተዳደሩ የእንስሳት ልማትና ልህቀት ማዕከል ኃላፊ ፀጋ ለማ(ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የማዕከሉ ኃላፊ ፀጋ ለማ(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቀደም ባሉት ዓመታት ለከተማ ግብርና ይሰጥ የነበረው ግምት ዝቅተኛ መሆን የሚፈለገው ውጤት እንዳይገኝ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል፡፡ አሁን ላይ ይህ አመለካከት እየተቀረፈ በመምጣቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማ ግብርና ስራ

‹‹በመዲናዋ እየተከናወነ ያለው ... ወደ ገጽ 4



## “ ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ብልጽግና ኢኖቬሽንን ማስፋፋት ወሳኝ ነው ”

- ሙፈሪሃት ካሚል
የሥራና ክህሎት ሚኒስትር

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ ኢንተርፕሪነሽፕና ኢኖቬሽንን ማስፋፋት ወሳኝ ነው ሲሉ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል ገለጹ።

16ኛው የዓለም ኢንተርፕረነርሺፕ ሳምንት

“ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ሀገራዊ ችግሮችን በምክክር ለመፍታት የምሁራን ድርሻ

**ታደሠ ብናልፈው**

**ዜና ትንታኔ**

ምሁራን በማስተማር፣ጥናትና ምርምር በማፍለቅ ለሀገር ግንባታ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡በተለይ ሀገራዊ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት መፍትሄ እንዲያገኙ መስራት ከእነሱ የሚጠበቅ ትልቅ ኃላፊነት ነው፡፡ ለሰላምና ለልማት እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን በዘላቂነት በመፍታት ሀገራዊ መግባባትን ለመፍጠርና የሚፈለገውን ዕድገት ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ግንባር ቀደም ሚና እንዳላቸውም ይገለጻል።

በኢትዮጵያ ለግጭት የሚዳርጓትንና ያለ መግባባታችን መንስኤ የሆኑትን ልዩነቶችን በምክክር ለመፍታት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ ኮሚሽኑ ችግሮችን በምክክር ለመፍታት በዘጠኝ ክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች ባደረገው የአጀንዳ ማሰባሰብና የምክክር መድረክ ከ105 ሺህ በላይ ማህበረሰቦች መሳተፍ መቻላቸውን የኮሚሽኑ መረጃ ያመለክታል፡፡



ከማህበረሰቡ የሚሰበሰቡ አጀንዳዎችም ትልቅ ትምህርት የሚሰጡ፤ ለሀገራዊ መግባባትና ዘላቂ ሰላም ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ናቸው ብሏል፡፡ በእነዚህ የምክክር መድረኮችም የምሁራን ተሳትፎ ጉልህ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ዘላቂ ሰላም ለማስፈን፣ ሀገራዊ መግባባትን ለማምጣትና አንድነትን ለማጠናከር የማህበረሰቡ ሚና እንዳለ ሆኖ የምሁራን ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ምሁራን በምርምራቸው፣ በመፍትሔ አፍላቂነታቸው፣ በእውቀታቸው፣ ሀገርን የሚጎዱ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት ሁነኛ መፍትሄ ለማምጣት ትልቅ አቅም

. ሀገራዊ ችግሮችን በምክክር.. ወደ ገጽ 4 ዞሯል






ሂሩት ካሳው (ዶ/ር)

## የሆቴል የባለሙያዎች አለባበስ ደንብ በአግባቡ ተፈጻሚ እንዲሆን የጋራ ኃላፊነት ያስፈልጋል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የሆቴልና መሰል ተቋማት የባለሙያዎች አለባበስ ደንብ በአግባቡ ተፈጻሚ እንዲሆን የጋራ ኃላፊነት ያስፈልጋል ሲሉ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ (ዶ/ር) ሂሩት ካሳው ገለጹ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ በሆቴልና መሰል ተቋማት ባለሙያዎች አለባበስ እና የመዋቢያ ጌጣጌጥ አጠቃቀም ደንብ አፈፃፀም ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትናንትናው እለት ተወያይቷል፡፡

የቢሮው ኃላፊ ሂሩት ካሳው (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ በሆቴልና መሰል ተቋማት የባለሙያዎች አለባበስ ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ የማህበረሰቡ እንዲሁም የውጭ ጎብኚዎች አጀንዳና ጥያቄ ሆኖ ቆይቷል። በዚህም ከተማ አስተዳደሩ ከፍትህ ቢሮ ጋር እንዲሁም ከተለያዩ የሆቴል ማህበራት ጋር በመሆን ደንቡ እንዲፀድቅ ተደርጓል።

በሆቴልና መሰል ተቋማት ባለሙያዎች አለባበስ እና የመዋቢያ ጌጣጌጥ አጠቃቀም ደንብ ወደ ትግበራ ሲገባ በቂ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እንደሚሰራ ገልጸው፤ ደንቡ በአግባቡ ተፈጻሚ እንዲሆን የጋራ ኃላፊነት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ደንቡ ዓለም አቀፍ መስፈርት (ስታንዳርድ) ላይ መሰረት ያደረገና ሙሉ በሙሉ ባህላችንን የሚጠብቅ መሆኑንም ገልጸዋል።

ደንቡን በተመለከተ ማብራሪያ የሰጡት የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎት ሰጪዎች አገልግሎት ምደባ ቡድን መሪ አቶ አምደ ማርያም ማሞ በበኩላቸው፤ በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩ ባለሙያዎች ወጥ የሆነ የአለባበስ፣ የጌጣጌጥ እና የመዋቢያ አጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት የሀገር ባልህና እሴት እንዲጠበቅ ለማድረግ ደንቡ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል በዘርፉ ተሰማርተው የሚሰሩ ሙያተኞች ሊደርስባቸው ከሚችለው አካላዊ፣ ሥነልቦናዊ ጫና እና አላስፈላጊ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችል መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ሆቴል ማኔጅመንት አሶሴሽን ጸሐፊ አቶ በሱፍቃድ ደባይ እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ በአሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፍ መድረኮችን የምታዘጋጅ ከተማ ሆናለች፡፡ በዚህም ሆቴሎች እንዲሁም መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሀገርን ገጽታ በሚገነባ መልኩ እንግዶችን ማስተናገድ ይኖርባቸዋል፡፡


ለዚህም የወጣው ደንብ የትኛውም አገልግሎት የሚሰጥ አካል ሥርዓትን የጠበቀና ኢትዮጵያዊነትን የሚያንጸባርቅ አለባበስና አጋጌጥ እንዲኖር የሚያደርግ ነው ብለዋል፡፡

ደንቡ የሀገር ባህልና እሴት እንዲጠበቅ ከማድረግ አንጻር ተስፋ ሰጪ ነው ያሉት አቶ በሱፍቃድ፤ ሆኖም ተፈጻሚነቱ ላይ ሁሉም አካል ጠንክሮ መስራት እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

# የፊልም ዘርፉ የሀገር ዋልታና ማገር እንዲሆን

**ሳሙኤል ወንደሰን**

**ዜና ሐተታ**





ሁሉም ኢትዮጵያዊ ምንም እንኳ የተለያየ ስሜትና ፍላጎት ቢኖረውም የሀገር ህልውና የሚፈታተኑ ሴራዎችን በማክሸፍ የኢትዮጵያን ሰላምና ክብር ማስጠበቅ የጋራ አጀንዳ ሊሆን ይገባል። ኪነ-ጥበብ የሕዝብ አንደበት እንደሆነ ሁሉ የፊልም ዘርፉም የሀገር ዋልታና ማገር ሆኖ እንዲያገለግል መስራት ያስፈልጋል።

ፊልም ባህልን ፣ ትውፊትን ለዓለም ሕዝብ ለማስተዋወቅ ይጠቅማል። በተለይ አሜሪካ፣ ህንድ፣ ኮሪያና ሌሎች በፊልም ኢንዱስትሪው ውጤታማ የሆኑ ሀገራት የዓለምን መጻኢ እጣ ፈንታ በፊልም እንዲንጸባረቅ በማድረግ የሀገራቸውን ገጹታ ከመገንባት ባሻገር ከፍተኛ ገቢ ሲያገኙበት ይስተዋላል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲኒማ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ሥራ አስኪያጅ አቶ ብርሃኑ ሚኔቶ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የፊልም ዘርፉ ባለሙያዎች በሀገራዊ ክብር ቁርጠኛ በመሆን የኢትዮጵያዊነትን ልዩ ገጹታ ማሳየት አለባቸው። ይህም ማህበራዊ ቀውስን ለማስወገድ፣ አንድነትንና ሰላምን ለማጽናትና መልካም ገጽታን ለተቀረው ዓለም ለማሳየት ጉልህ ድርሻ አላቸው።

ዘርፉን ለትውልድ እድገትና ለሀገር ግንባታ መጠቀም ያስፈልጋል። ይህም ባህል፣ እሴት፣ አንድነት እና ሰላምን ከመጠበቅ አንጻር ከፍተኛ ሚና አለው ያሉት አቶ ብርሃኑ፤ የፊልም ዘርፉ ያለውን አወንታዊ ሚና አሟጦ ለመጠቀም በቅንጅት መስራት እንደሚገባ ተናግረዋል።

ፊልም የኅብረተሰቡን እሴት ወደ ተንቀሳቃሽ ምስል ተቀይሮ የሚቀርብበት ነው። ለምሳሌ ድህነት የኅብረተሰቡ ዐብይ ችግር ከሆነ እንዴት ድህነትን ማሸነፍ እንደሚቻል ያሳያል ያሉት አቶ ብርሃኑ፤ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሃሳቦችን ይዘው የሚሰሩ ፊልሞች ለሀገር ግንባታ ወሳኝነት አላቸው ብለዋል።

የአሜሪካ፣ የህንድና የሌሎች ሀገራት ፊልሞች ገቢን በማስገኘትና ኅብረተሰብን በመቅረፅ ረገድ ያላቸው ሚና ትልቅ መሆኑን ገልጸው፤ የሀገራችን የፊልም ኢንዱስትሪ በሚጠበቅበት ደረጃ ልክ እንዲያድግ የዘርፉ ባለሙያዎች የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ በመቅሰም ዘርፉን ማሳደግ እንደሚኖርባቸው ገልጸዋል።

ፊልምን ለሀገር ግንባታ ለማዋል መሰጠትን ይጠይቃል። የሀገር ቁጭት በውስጥህ ካለ በርካታ ለፊልም የሚሆኑ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮች መኖራቸውን የገለጹት አቶ ብርሃኑ፤ የዜጎች አንድነት፣ መተማመን፣ መፋቀርና ህብረትን የመመስረት ጉዳይ ድንቅ ፊልም ለመስራት ያስችላል ነው ያሉት።

ሀገር ግንባታ ውስጣዊነትን ይጠይቃልና ኃላፊነት በተሰማው መንገድ ከተሠራ ሀገር መለወጥ ይቻላል። በዚህ ረገድ ድርጅቱ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር ልምዶችን የማስተላለፍ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንደሚገኝ ገልፀው፤ ከዘርፉ ባለሙያዎች ጋር በትብብር የመሥራት ፍላጎት መኖሩን ተናግረዋል።

ሕዳር 8 ቀን 2017 ዓ.ም የዛሬ 34 ዓመት የተሰራው "አስቴር" ፊልም ከ35 ሚሜ ተንቀሳቃሽ ምስል ወደ ዲጂታል ፊልም ተቀይሮ በከንቲባ አዳነች አቤቤ ተመርቆ ለዕይታ በቅቷል። ከንቲባ አዳነች አቤቤ በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ወቅት እንደገለጹት፤ ጥበብ የእድገታችን እና የታሪካችን ማሳያ በመሆኑ በሀገር ግንባታና በማህበራዊ ህይወታችን ውስጥ የአንድነትና የአብሮነት ማሳያ አድርጎ መጠቀም ይገባል ብለዋል።

ጥበብ ትናንትን ከዛሬ ጋር ማያያዝ ይችላል ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ "አስቴር" የተሰኘውን ፊልም ከዛሬ ህይወታችን ጋር እያስተሳሰርን ማየት አለብን። በዚህም ከትናንት ስህተት መማርና ጠንካራ ጎኖችን ደግሞ አጠናክሮ መቀጠል ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

በ1983 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፊልም ኮርፖሬሽን አማካኝነት ሀገራዊ ዘውግ ላይ ተንተርሶ የተሰራውና "አስቴር" የተሰኘው ኢትዮጵያዊ ፊልም፣ የአጻጻፍ ደረጃው ከፍ ያለና ከድርሰት እስከ ፕሮዳክሽን ድረስ ሙሉ በሙሉ በሀገር ባለሙያዎች የተሰራ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

እንደ ከንቲባ አዳነች ገለጻ፤ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም በዓድዋ ሲኒማ በሀገራችን የመጀመሪያውን ባለ ቀለም ፊልም "አስቴር "የተሰኘውን ዲጂታላይዝ በማድረግ የሀገራችን አንጋፋ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችና ተጋባዥ እንግዶች በታደሙበት በይፋ መርቀን ከፍተናል ነው ያሉት።

ጥበብ ሀገርን በማነፅ ጉዞ ውስጥ አይነተኛ ሚና አላት። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ዘርፉ የሀገራችንን የልዕልና ጉዞ ሊያሳልጥ እንዲችል የኪነ-ጥበብ መሰረተ ልማቶችን ገንብቶ ለሕዝቡ ጥቅም አቅርቧል። ይበልጥ የማስፋፋቱን ስራም አጠናክረን የምናስቀጥል ይሆናልም ብለዋል።

የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሒሩት ካሳው (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ቢሮው የፊልም ሥራዎችን ከሦስት ዓመታት ወዲህ ከሀገር ውጭና በሀገር ውስጥ በማፈላለግ ዲጂታላይዝድ እንዲሆኑ እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ቆየት ባሉ ፊልሞች የቀደመውን ማህበረሰብ የባህል ትስስር ለመዳሰስና ዛሬ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመለየት እንደሚረዱ ገልጸው፤ ቢሮው ከዚህ በፊት የመጀመሪያውን ባለ ነጭና ጥቁር ቀለም "ሒሩት አባቷ ማነው?" የተሰኘ ፊልም በድጋሚ ለዕይታ እንዲበቃ ለሲኒማ ቤቶች አስተዳደር አስረክቧል ብለዋል።

"አስቴር" ፊልም የአንድ ወጣ ሴት የህይወት ውጣ ውረድ የሚያሳይ ፊልም ነው። ፊልሙ በዘመኑ በተለያየ የኑሮና የትምህርት ደረጃ ያሉ የትዳር አጋሮች የሚደርስባቸው ጫናን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ፊልሙ ከ35 ሚሊሜትር በቀላሉ ከዘመኑ ጋር እንዲሄድ ተደርጎ ለትውልድ እንዲተላለፍ ተደርጓል።

በቀጣይ ፊልሙ በመንግሥት ሲኒማ ቤቶች ለዕይታ ከበቃ በኋላ በሀገራችን በተለያዩ ከተሞችና ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም በውጭ ሀገር በተለያዩ ከተሞች ለዕይታ ይቀርባል። ለኢትዮጵያ ፊልም ኢንዱስትሪ እንደ አንድ የመሰረተ ድንጋይ የሚታሰበው "አስቴር" ፊልም በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ተሳትፎ በኢትዮጵያ ፊልም ኮርፖሬሽን የተሰራ ነው።

# ባዛሩ ለዕደ ጥበብ ውጤቶች የገበያ ትስስር የሚፈጥር ነው

**ታደሠ ብናልፈው**



አዲስ አበባ፡- የንግድ ትርዒቱና ባዛሩ የሀገር ውስጥ ምርታማነትን የሚያሳድግ፣ ለዕደ ጥበብ ውጤቶች የገበያ ትስስር የሚፈጥር መሆኑ ተገለጸ።

በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል «ሀገራዊ መግባባት ለህብረ ብሔራዊ አንድነት» በሚል መሪ ቃል የ19ኛው የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀንን የተመለከተ የንግድ ትርዒትና ባዛር እየተካሄደ ነው።

የንግድ ትርዒትና ባዛሩን በንግግር የከፈቱት የአዲስ አበባ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልከድር፤ የ19ኛውን የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀንን አስመልክቶ የተዘጋጀው የንግድ ትርዒትና ባዛር የሀገር ውስጥ ምርትና ምርታማነት የሚያሳድግ፤ ለዕደ ጥበብ ውጤቶችም የገበያ ትስስር የሚፈጥር ነው።

የንግድ ትርዒቱና ባዛሩ በመንግሥት አነሳሽነትና አስተባባሪነት የተደረገ እንደሆነ የገለጹት አፈጉባኤ ቡዜና፤ ወጣቶች የፈጠራ እውቀትና ክህሎታቸውን ተጠቅመው ያመረቷቸው ልዩ ልዩ ምርቶችንና የዕደጥበብ ውጤቶችን ለተጠቃሚ ማህበረሰብ በማስተዋወቅ የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው እድል የሚሰጥ ነው ብለዋል።

19ኛውን የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ቀን አስመልክቶ የተዘጋጀው የንግድ ትርዒትና ባዛር ኢትዮጵያ ያላትን ብዝሀ ፀጋ እንድታለማ፤ የሀገር ውስጥ ምርትና ምርታማነትን እንድታሳድግ እንዲሁም ለዕደ ጥበብ ውጤቶች የገበያ ትስስር እንዲፈጠር የሚያበረታታ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የንግድ ትርዒቱና ባዛሩ ባህልን ከማስተዋወቅ ባለፈ የተለያዩ እሴቶችን በመጨመር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማሳለጥ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን አመልክተው፤ የባህል፣ የቁስና የመንፈሳዊ ፀጋዎችን በማልማት፣ ቱሪዝሙን በማስፋፋትና ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር ሀገራዊ ኢኮኖሚን ለማሳደግ እየተሰራ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ባዛሩ ስራ ፈላጊዎችና ፈጣሪዎች ልምድ እንዲለዋወጡ፤ አዳዲስ ሃሳቦች እንዲያመነጩ የሚያነሳሳና ኢንቨስትመንት ለመሳብ ትልቅ ጠቀሜታ አለው ብለዋል።

የኢንዱስትሪው ዘርፍ በማልማት ከመስኩ የሚገኘውን ገቢ ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው፤ ከዘርፉ መገኘት የሚገባውን ጥቅም ለማግኘትም የለውጡ መንግሥት እየሰራበት ይገኛል ሲሉ ጠቁመዋል።

ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶች፣ ባህሎች የሀገር ምንዳዎች ናቸው፤ የሀገር ምንዳ የሆኑ የብዝሃ ፀጋዎችን አልምቶ ሁለተናዊ እድገትን በማረጋገጥ ሁሉንም ማንነቶች ያቀፈ እውነተኛ ህብረ ብሔራዊ ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶሚ አበበ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የብሔር ብሔረሰቦችን ቀን ለማክበር ከሚከወኑ ክንዋኔዎች ውስጥ የንግድ ትርዒትና ባዛር አንዱ ነው፤ በክንዋኔውም ኢንዱስትሪያኒስቶች፤ ኢንተርፕራይዞች፣ የሀገር ውስጥ ምርቶችንና የዕደጥበብ ምርቶችን ከተጠቃሚ ማህበረሰቡ ጋር ይተዋወቃሉ።

19ኛውን የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ምክንያት በማድረግ እየተካሄደ ያለው የንግድ ትርዒትና ባዛር የሀገር ውስጥ ምርቶችን በሚፈለገው ልክ እንዲያድጉ የሚያበረታቱበት፣ የዕደጥበብ ውጤቶች ለገበያ የሚተዋወቁበት ነው ብለዋል።

19ኛውን የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ምክንያት በማድረግ በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል እየተካሄደ ባለው የንግድ ትርዒትና ባዛር 150 ተሳታፊዎች እየተሳተፉ እንደሚገኝ ታውቋል።



# በዞኑ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የግብርና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራዎች እየተሠሩ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

ጂንካ፡- ቴክኖሎጂን በመጠቀም የግብርና ምርታማነትን የማሳደግ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን የአሪ ዞን አስታወቀ።

አሪ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ አብረሃም አታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሪ ዞን በግብርናው ዘርፍ ብዙ ጸጋዎች አሏት። በዋናነት ቡና፣ ኮረሪማና ቀይ ቦሎቄና ሌሎች ምርቶች በስፋት የሚመረቱበት ዞን ነው። የተለያዩ ሰብሎችን ምርታማነት ለማሳደግ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት እየተጠቀምን ነው ብለዋል። እንዲሁም የክልሉ የግብርና ምርምር ማእከል የምርምር ስራዎችን በመስራት የቁም እንስሳት ውጤታማነትን የማሳደግ ስራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አስተዳዳሪው ገለጻ፣ በአሪ ዞን ላይ እየተሰሩ ያሉ የተለያዩ የቴክኖሎጂና የተሻሻሉ የሩዝ፣ በቆሎ፣ ስንዴ እና አደንጓሬ የዘር ብዜት ስራዎች መኖራቸውን ገልጸዋል። በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በግብርናው ዘርፍ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ስራዎች ህብረተሰቡን በማስተባበር ባለፉት ጊዜያት የተሰሩ ስራዎች እጅግ አመርቂ ውጤት አምጥተዋል። የግል አልሚዎች በግብርናው ዘርፍ በስፋት እንዲሰማሩ የማድረግ ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን፤ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ልምድ እያደገ መጥቷል። በግብርና በእርሻ ዘርፍ በግብርና ማቀነባበሪያ ለሚሰማሩ አልሚዎች በዞኑ በበቂ ሁኔታ የተዘጋጁ መሬቶች መኖራቸውን ገልጸዋል።

በግብርናው ዘርፍ መሰማራት ለሚፈልጉ ኢንቨስተሮች በተቀላጠፈ ሁኔታ የመሬት አቅርቦት እየተዘጋጀ ነው ያሉት አቶ አብረሃም፣ በዞኑ ውስጥ ለኢንቨስትመንቱ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር መሰረተ ልማቶች የማስፋት ስራዎች እየተሰሩ ነው። ዞኑ ከግብርና ጐን ለጐን ከፍተኛ የቱሪስት መስህብ መዳረሻ በመሆኑ በሆቴልና ቱሪዝም መስክ መሰማራት ለሚፈልጉ ኢንቨስተሮች ዞኑ ዝግጁ ነው ብለዋል።

የዞኑ ምክትል አስተዳዳሪና የግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ ታፈሰ ተስፋዬ በበኩላቸው፣ ዞኑ አዲስ እንደመሆኑ የምርጥ ዘር ችግር ነበረበት። ይህን ችግር ለመቅረፍ ከአርሶ አደሮች ጋር በመሆን የሩዝ፣ በቆሎ፣ ስንዴና የአደንጓሬ ዘር በኩታ ገጠም የብዜት ስራዎች እየተሰሩ ነው ብለዋል። የበቆሎ የምርጥ ዘር ማባዣው ጣቢያ በኩታ ገጠም በ15 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ነው፣ ዞኑን በግብርና እራሱን ለማስቻል ያግዛል።

በአሪ ዞን ከበቆሎ ምርጥ ዘር ማባዣ ጐን ለጐን በ75 ሄክታር መሬት ላይ የስንዴ ምርጥ ዘር ማባዣ ጣቢያ አለ ያሉት የግብርና ቢሮ ኃላፊው፤ በቀጣይ የዞኑ አርሶ አደሮች በሁሉም የሰብል አይነቶች የምርጥ ዘር ችግር እንዳይገጥማቸው እየተሰራ ነው። የዘር አቅርቦት ችግርን ሙሉ ለሙሉ ለመቅረፍ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

# በአዲስ አበባ 154 ሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት የኑሮ ውድነትን የማረጋጋት ሥራ እየሠሩ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ 154 ሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት የኑሮ ውድነትን የማረጋጋት ሥራ እየሰሩ እንደሚገኝ የከተማው ህብረት ሥራ ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

በኔዘርላንድ የተደረገውን የህብረት ሥራ ማህበራት የሥራ ጉብኝት ተከትሎ በከተማው ከሚገኙ ህብረት ሥራ ማህበራት፣ዩኒየኖችና ሠራተኞች ጋር የፓናል ውይይት ትናንት ተደርጓል፡፡



ኮሚሽነር ልዕልቲ ግደይ



አቶ አብዲ ሙመድ

የአዲስ አበባ ህብረት ሥራ ኮሚሽነር ልዕልቲ ግደይ በመድረኩ ላይ እንደተናገሩት፤ በአዲስ አበባ 154 የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት የኑሮ ውድነትን የማረጋጋት ሥራ እየሠሩ ነው፡፡

የከተማው ህብረት ሥራ ኮሚሽን ዘጠኝ ሺህ ማህበራት ያሉት ሲሆን፤ አንድ ሺህ 600 የቁጠባ ማህበራት መሆናቸውን የገለጹት ኮሚሽነሯ፣154 የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራትና 11 ዩኒየኖች በከተማው የተለያዩ ምርቶችን ለሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የዋጋ መረጋጋት ሥራ እየሠሩ ይገኛል ብለዋል፡፡

ማህበራቱ የትኩረት አቅጣጫቸው ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት መሆኑን ጠቅሰው፤ በማምረትና እሴት ጨምሮ መሥራት ላይ ቀሪ ሥራ እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል፡፡

የህብረት ሥራ ማህበራት ምርትን ከአምራቹ በቀጥታ በማምጣት ከነጋዴው በቀነሰ መልኩ ለህብረተሰቡ እንደሚያቀርቡ ገልጸው፤ የኢንዱስትሪና የግብርና ምርቶችን ከነጋዴው በዋጋ በቀነሰ መልኩ እያቀረቡ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

በእሁድ ገበያዎች ላይ አምራቾች፣ማህበራት፣ነጋዴዎች ምርቶችን እያቀረቡ ይገኛል ያሉት ኮሚሽነር ልዕልቲ፣በእሁድ ገበያ ተደራሽነትን ማስፋትና የአቅርቦት አማራጭን የማብዛት ሥራ በመሥራት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

በከተማዋ በ800 የመቸርቸሪያ ሱቆች ላይ የሚቀርቡ የተወሰኑ ምርቶች ላይ ከእሁድ ገበያ ዋጋ ለውጥ ሊኖራቸው እንደሚችል ጠቅሰው፣ማህበራቱ ለህብረተሰቡ አማራጭ ገበያ ሆነው መቅረባቸውና የግብርና ምርቶች በሱቆችና ወፍጮ ቤቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረቡ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

የህብረት ሥራ ማህበራት የዘመኑ አሠራር ሥርዓትን በመዘርጋት ለማህበረሰቡ ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው በመግለጽ፤ የውስጥ አቅምን በመጠቀም ወደ አምራችነት መሸጋገር፣ተደራሽነትን ማስፋትና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት እንደሚጠበቅባቸው ጠቁመዋል፡፡

የህብረት ሥራ ማህበራት ግላዊ ጥቅም ማካበቻ ሳይሆኑ ለህብረተሰቡ የተሻለ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ እየተሰራ መሆኑን አመልክተው፣የከተማ አስተዳደሩ ለማህበራቱ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ የአሰራር ሥርዓቶችን ማስተካከሉን ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አብዲ ሙመድ በበኩላቸው፣ኮሚሽኑ ለማህበራቱ የአሰራር ሥርዓቶችን፣ፖሊሲን፣ስትራቴጂን፣ገበያ የማፈላለግ፣ አቅም ግንባታና የውጭ ተሞክሮዎችን የማስፋት ሥራዎችን ይሠራል፡፡

ኔዘርላንድ በህብረት ሥራ ማህበራት በኩል ከድህነት ወደ ብልጽግና መሸጋገር ችለዋል ያሉት አቶ አብዲ፤ በሀገሪቱ የተገኘውን መልካም ተሞክሮ እንደሀገሪቱ ሁኔታ ወደ ተጨባጭ ሁኔታ በመለወጥ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ያላትን የተሻለ የተፈጥሮ ጸጋ ፣አምራች ሀይልና ሌሎች መልካም እድሎች መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ማህበራትን በማጠናከር ለዜጎችና ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ማዋል አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# ልቆ መገኘት አሸልሟል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

**ዜና ሐተታ**



አዳራሹ በሰው ተሞልቷል፤ በርከት ያለው ሰው የዕለቱን “ክብር ለጥበብ የተሰኘ መርሃግብር” እንዲከታተል የተጋበዘ ሲሆን፣ በቁጥር ጥቂት የሆነው ደግሞ ለሽልማት በበቃው የተለያየ የሙያ ዘርፍ አንዱ በሆነው በሰራው የላቀ ስራ ተመርጦ እውቅና ሊሰጠው የታደመ ነው። ለሽልማት ከበቁ የሙያ ዘርፎች መካከል ደግሞ ሙዚቃ፣ ስዕል፣ ሰርከስ እና ሌሎች የጥበብ ስራዎች ተጠቃሽ ናቸው። በአብላጫነት የተሻለ እንቅስቃሴ ያሳዩ አካላት የዕለቱን ሽልማት ለመቀበል ችለዋል።

ይህ ሰሞኑን በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አዘጋጅነት የቀረበው አራተኛው ክብር ለጥበብ የተሰኘ መርሃ ግብር ድንቅ ስራ ለሰሩ የኪነ ጥበብ ሰዎች ዕውቅናና ሽልማት የሰጠ ሲሆን፣ መርሃ ግብሩ ላይ ከሁሉም ክልሎች የተወጣጡ 67 ተሸላሚዎች መመረጣቸውን ለማወቅ ተችሏል፤ ሌሎች ስድስት ልዩ ተሸላሚዎች ደግሞ የክብር ዕውቅና ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

በዕለቱ ከተሸለሙት መካከል ቀሲስ ረዳኢ ኃይሉ አንዱ ናቸው፤ የመጡበት አካባቢ ትግራይ ክልል መቐለ፣ ኲሐ ክፍለ ከተማ መሆኑን ይናገራሉ። ቀሲስ፣ ለሽልማት ያበቃቸው ስራ ጥንታዊ እደ ጥበብ የሆነው የሽመና ስራ መሆኑን ያስረዳሉ።

ከገጠር ወደ ከተማ ትምህርት ለመማር እና የበለጠ ኑሮ ለማሻሻል መምጣታቸውን የገለጹልን ቀሲስ ረዳኢ፣ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ በመንግሥት መስሪያ ቤት ተቀጥረው ቢሰሩም፤ ውስጣቸው የነበረው የሽመና ጥበብ ፍላጎት ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በፍቅር የሚሰሩት ስራ መሆኑን ያስረዳሉ።

እርሳቸው የሚሰሩት የሽመና አልባሳት በእንደርታ እና በራያ አካባቢ የሚለበስ የባህል ልብስ ቦፌ፣ድርበድር፣ ዝርዝር፣ ፈትል እና ሌሎች በርካታ ባህላዊ አልባሳት ጥበብ በማላበስ እና አዳዲስ ፈጠራዎችን በመጨመር ለገበያ እንደሚያቀርቡ ይናገራሉ።

ቀሲስ ረዳኢ፣ መንፈሴ እየተደሰተ ከሙያው በማገኘው ገቢ ምድራዊ ለሆነው ኑሮዬ እጅግ አስፈላጊ የተባሉት ነገሮች ማለትም ዘመናዊ ቤትና መኪና ገዝቻለሁ ይላሉ። የመጀመሪያ ልጃቸው ሙያውን አስተምረውት የአምስት ዓመት ዕቅድ በማውጣት የራሱ መኪና መግዛቱን ይናገራሉ። እንዲሁም ሌሎች ተቀጥረው እየሰሩ እንዲጠቀሙ አስተዋፅኦ ማድረጋቸውንም ያስረዳሉ።

“መንፈስ እና ስጋ ማዋደድ የሚቻለው በጥበብ ነው።” ያሉት ቀሲስ ረዳኢ፤ ስጋችን ከመንፈሳችን ጋር ሚዛን አስጠብቀን በመታዘዝ ድንቅ የሆነ አዳዲስ ፈጠራ በተደጋጋሚ እና በዘላቂነት ስንተገብር የኪነ ጥበብ ዋነኛ ምልክት መሆኑን ለማወቅ እምነታችን ያስረዳናል ይላሉ።

ከመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅስ መካከል ቅዱስ ጳውሎስ፤ ‘ሊሰራ የማይወድ ቢኖር አይብላ’ ይላል ያሉት ቀሲሱ፣በቤተ መቅደስ እና በሌሎች ተቋማት ተቀጥሬ ከምጠብቀው ወርሃዊ ደመወዝ ይልቅ በነፃነት እና በደስታ የምሰራው የጥበብ ሙያ እጅጉን ይበልጥብኛል ሲሉ ይናገራሉ። መርሃ ግብሩ ላይ ለተደረገላቸው የሽልማት እና የዕውቅና ስጦታ እጅጉን መደሰታቸውንም ይገልፃሉ።

ኪነ ጥበብ ለሀገር እድገት ዋነኛው ነው ያሉ ሲሆን፤ ሰርተን በምናገኘው ገቢ ግብር ለሀገር መክፈል ያስደስተኛል ሲሉ ያስረዳሉ፤ በመሆኑም ለረጅም ዓመታት ግብር መክፈል በሚጀመርበት ቀን ሐምሌ አንድ ቁጥር አንድ የመጀመሪያው ግብር ከፋይ እርሳቸው መሆናቸውን በኩራት ይናገራሉ።

በተመሳሳይ በዚሁ መርሃ ግብር ልዩ ተሸላሚ ከሆኑት መካከል በማስታወቂያ ስራ ለረጅም ጊዜ ታዋቂነትን እና ተወዳጅነትን ያተረፉት አርቲስት ሰራዊት ፍቅሬ እና ሙሉአለም ታደሰ ተጠቃሽ ናቸው። አርቲስት ሰራዊት ፍቅሬ መርሃ ግብሩ ላይ ተገኝቶ ሽልማቱን ተቀብሏ። በተደረገው የዕውቅና እና የሽልማት ስጦታ እጅግ መደሰቱን ገልጿል። እስከ ዛሬ በማስታወቂያ ዘርፍ የዕውቅና ሽልማት ሳይደረግ አሁን መደረጉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሊመሰገን እንደሚገባው ተናግሯል።

በመርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ፣ ለታዳሚዎች እና ለተሸላሚዎች የጥበብን ታላቅነት ገልጸዋል። ሚኒስትሯ፣ ለጥበብ ክብርም ትኩረትም እንደሚሰጠው አስረድተዋል። በሁሉም የሀገሪቱ ማዕዘን ለሚገኙ የኪነ ጥበብ ሰዎች እና የጥበብ ወዳጆች የኪነጥበብ ዘርፍ ወንድማማችነት እና እህትማማችነት ለማጠናከር ሙያዊ ተሳትፎ ሊጠነክር እንደሚገባም አመልክተዋል።

ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡ ዘርፈ ብዙ ባለሙያዎች በተለያዩ የሙያ ዘርፎች እና ሌሎች የጥበብ ስራዎች በአብላጫነት ያሳዩ ተሸላሚዎች ሽልማታቸውን ወስደዋል።

# ‹‹በመዲናዋ እየተከናወነ ያለው…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በሌሎችም ከተሞች ተምሳሌት የሚሆን ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡

ያለንን አቅም በአግባቡ ጥቅም ላይ ባለማዋላችን በእንስሳት ተዋጽኦ ዋጋ መናር ማህበረሰቡ ሲፈተን መቆየቱን አስታውሰው፤ እንደ ሀገር ለከተማ ግብርና በተሰጠው ትኩረት እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ጥሩ ውጤት እያስገኙ ነው፡፡ ይህም ገበያው እንዲረጋጋ በማድረግ የነዋሪውን የኑሮ ጫና ከማቅለል አንጻር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ብለዋል፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ ከእንስሳት እርባታ ጋር በተያያዘ የተዛባ አስተሳሰብ እንደነበር አስታውሰው፤ በተሠራው የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ከዚህ በፊት የነበሩ አመለካከቶች ተቀይረው አሁን ላይ በርካታ ዜጎች ሥራው ላይ ተሠማርተው እንደሚገኙ አብራርተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ በከተማ ግብርና ለሌሎችም ከተሞች ምሳሌ የሚሆን ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ የራስን የምግብ ፍላጎት ከማሟላት አልፎ ወደ ገበያ በማቅረብ ለገበያ መረጋጋት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የከተማ ግብርና በአነስተኛ ቦታ መከናወን የሚችል መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ፀጋ፤በልማት የሚነሱ አርሶ አደሮች፣ ወጣቶች እና የቤት እመቤቶች እየተደራጁ



በአነስተኛ ቦታዎች ላይ ከተማ ግብርናን እየሠሩ ውጤታማ መሆን ችለዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የሥራ እድል ፈጠራ ሥራዎች በአምራች ዘርፉ ላይ ትኩረት ያደርጉ እንደነበሩ አስታውሰው፤ አሁን ላይ የከተማ ግብርና የብዙዎች የሥራ እድል እና የሀብት ምንጭ መሆን መቻሉንም ገልጸዋል፡፡

የዘርፉን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በመንግሥት በኩል ሥራውን በቴክኖሎጂ የመደገፍና የምርጥ ዘር አቅርቦት ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይነትም ከግብዓት አቅርቦትና በተለይም ከእንስሳት መኖ ዋጋ መናር ጋር ተያያዞ የሚነሱ ችግሮችን ለመቅረፍ በትኩረት እንደሚሠራ ኃላፊው ጨምረው ገልጸዋል፡፡

# ‹‹በመንግሥት የፕሮጀክት…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ኢትዮጵያ እምቅ አቅም ያላት ትልቅ ሀገር ናት ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የሚጠበቅብን ያላትን አቅም ማወቅና ጥቅም ላይ ማዋል ነው፡፡ይህም የምናልማትንና የምናስባትን ኢትዮጵያ ለልጆቻችን ለማስረከብ በር የሚከፍት ነው ፡፡መልካም ልምዶችን ማጠናከርና በትብብር መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የሀገር ውስጥ የግሉ ዘርፍ ምርታማነት ሀገራዊ የኢንዱስትሪ ልማታችንን ከግብ ለማድረስ እና ኢኮኖሚያችንን ለማጠናከር ወሳኝ ሚና ይጫወታል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ የግል ዘርፉ ከሌብነት፣ በአቋራጭ ለመክበር ከመሞከርና ግብር ከመሰወር ወጥቶ ትልልቅ ሥራዎች ላይ ማተኮር ይኖርበታል፡፡ በዚህም ሀገር በመገንባት ሂደት ውስጥ የሚጠበቅበትን አወንታዊ ሚና እንዲጫወት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ባለሀብቶች እና በየደረጃው ያሉ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎች ሀገር የሚለውጥ ሥራ ላይ ትኩረት አድርገው መሥራት እንዳለባቸው ጠቁመው፤ ባለፉት ዓመታት በግብርናው ዘርፍ የተመዘገበውን አመርቂ ውጤት በአምራች ዘርፉ እንዲደገም በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ስትሪንግ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

ህልማችን ትልቅ ነገር እያሰብን ከትንሹ ተነስተን በፍጥነት ትልቁ ላይ መድረስ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኢንዱስትሪ ፓርኮቻችን የጀመርንበትና የሠራንበት ሁኔታ ችግር ያለበት ነው፡፡ ኢንዱስትሪ ፓርኮቻችንም አንድ ቢሊዮን ዶላር ገደማ እዳ አለባቸው፡፡ ይህን ሁኔታ መቀየርና በሀገር አቅም ትልልቅ ሥራዎችን መሥራት እንደሚቻል ያሳዩ ባለሀብቶችን ልምድ አስፍቶ መሄድ እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ነው፡፡ ሀገራዊ ጥቅል ምርት በአምስት ዓመታት ውስጥ በእጥፍ አድጓል፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከሰሀራ በታች በሚገኙ አፍሪካ ሀገሮች ትልቁ ኢኮኖሚ ሆኗል፡፡ይህም የኢትዮጵያ የመነሳት ጊዜ እውን እየሆነ መምጣቱን የሚያመላክት ነው፡፡

ሁላችንም በትብብር ያለንን አቅም አስተባብረን ሀገር የሚቀይርና ለብዙዎች የሥራ እድል የሚፈጥር ሥራ ለመሥራት መትጋት እንደሚገባም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# “ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በኢትዮጵያ "ኢንተርፕረነርሺፕ ለሁሉም" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት መካሄድ ጀምሯል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ ኢንተርፕሪነሽፕና ኢኖቬሽንን ማስፋፋት ወሳኝ ነው።

ኢንተርፕረነርሺፕ የዜጎችን፣ የተቋማትን፣ የሀገርንና የዓለምን ታሪክ የሚቀይር በመሆኑ ለሁሉም ተደራሽ የምናደርገው እና ዓመቱን ሙሉ የምንሰራበት ተግባር ነው ብለዋል።

ኢንተርፕሪነርሽፕና ኢኖቬሽን የዘመናችን ሁነኛ የልማት መሳሪያዎች ናቸው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ለኢትዮጵያ የሚሆን የኢንተርፕረነርሺፕና የኢኖቬሽን ስነ ምህዳር ለመፍጠር በትብብር መስራት እንደሚገባም አስታውቀዋል።

ኢንተርፕረነርሺፕ ለሀገር ኢኮኖሚ ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ ባለፈ ከዓለም ሀገራት ጋር የሚያስተሳስረን ቁልፍ ዘርፍ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እውቀትና ፈጠራ መር የሆነ ኢኮኖሚ ለመገንባት ኢንተርፕረነርሽፕ ተቋማዊ መልክ ይዞ እንዲሄድ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አቅጣጫ መሰጠቱን አስታውሰው፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በዘርፉ ባለፉት ሁለት ዓመታት በተሰሩት ስራዎች ትልቅ መነቃቃት መፈጠሩን ገልጸው፤ በአንድ ጊዜ ሶስት ሺህ የሚደርሱ ዜጎች የፈጠራ ሀሳብ ውድድር እያደረጉ መሆኑን አስረድተዋል።

በሌላ በኩል ዓለም አቀፉ የአንተርፕሪነርሺፕ ሳምንት የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና የኢንተርፕሪነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት ከሌሎች አጋር ተቋማት ጋር በመተባበር በግንዛቤ ማስጨበጫና መረጃ ሰጪ በሆኑ የተለያዩ ዝግጅቶች እንደሚያከብሩት አመላክተዋል።

የአንተርፕሪነርሺፕ ሳምንቱ ስራ ፈጣሪዎችን፣ ባለሀብቶችን፣ የፖሊሲ አውጪዎችን፣ ተመራማሪዎችን፣ ደጋፊ ድርጅቶችን እና ሌሎች የምጣኔ ሀብትና ፈጠራ ስራን ለማሻሻል ድጋፍ የሚያደርጉ ተባባሪ አካላትን የሚያሳትፍ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የኢንተርፕረነርሺፕ ሳምንት በፖለቲካና ኢኮኖሚ ያደገች እና የተለወጠች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ያግዛል።

ኢንተርፕረነርሺፕ ለሀገር እድገት ወሳኝ መሆኑን ካደጉት ሀገራት መማር ይቻላል ያሉት ሚኒስትሩ፤ መንግሥትም ለዘርፉ ምቹ ምህዳርን ለመፍጠር እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

ስራ ፈጣሪዎችን የሚያበረታታ እና የፈጠራ ሃሳባቸውን ወደ ተግባር መቀየር የሚያስችል የፖሊሲ ማሕቀፍ መዘርጋት እንደሚገባም አስታውቀዋል።

# ሀገራዊ ችግሮችን በምክክር…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አላቸው፡፡ ሰሞኑን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የምሁራን ሀሳብ በአጀንዳ ማሰባሰቡና በምክክር መድረኩ ለማካተትና የሚጨበጥ ውጤት ለማምጣት ህዳር 6 ቀን 2017 ዓ.ም ከ56 ዩኒቨርሲቲዎች ከተውጣጡ ሊሂቃንና የተማሪ ተወካዮች ጋር ምክክር አድርጓል፡፡

ሀገራዊ መግባባትን ለማምጣት ሰላማዊ፣ ሀገር ወዳድ፣ ምክንያታዊ ትውልድ ማፍራት፣ የተሳሳተ ትርክትን ማረም አስፈራጊ ነው፡፡ ሰላማዊ፣ ሀገር ወዳድ፣ምክንያታዊ ትውልድ ለማፍራትም ሆነ የተሳሳተ ትርክትን ለማረም ደግሞ ምሁራን ያላቸው ሚና ትልቅ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የሚስተዋለውን አለመግባባትና ግጭት ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኝ ለማድረግ የምክክር ኮሚሽኑ እየሰራ ባለው ስራ ምሁራን ምን ዕይታ አላቸው? ሀገሪቱ እየገጠማት ያለውን ችግር ለመፍታትስ የምሁራን ሚና ምንድ ነው? በሚሏቸው ጉዳዮች ምሁራን አስተያየታቸውን ሰጥተውናል፡፡

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የጽህፈት ቤት ኃላፊ መለሰ ጥፉ፤ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከተቋቋሙ ጀምሮ ሀገራዊ መግባባትን ለማምጣት በርካታ ስራዎችን ሰርቷል፤ አሁንም እየሰራም ነው፤ ግጭትና አለመግባባት እያመጡ ያሉ ጉዳዮችን ነቅሶ ለማውጣት ታች ወርዶ ከማህበረሰቡ ጋር እያደረገ ያለው ውይይት የሚበረታታ ነው ይላሉ፡፡

ኮሚሽኑ ለሀገር ሰላምና እንቅፋት ፀር የሆኑ ችግሮችን ነቅሶ ለማውጣትና ሰላምን ለማምጣት ከዩኒቨርሲቲ ምሁራን፣ ከመምህራን፣ ከሰራተኞች፣ ከተማሪዎችና ከማህበረሰቡ ጋር በርካታ ውይይቶችን አድርጓል፤ ውይይቱም ቀድመው የነበሩ አሉታዊ ትርክቶችን በማረምና የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ የሚያስችል መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በሀገር ደረጃ የሚደረግ ምክክር በርካታ ችግሮችን ወደ አንድ አምጥቶ፤ የጋራ አጀንዳን ለመቅረፅ፣ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ያስችላል፤ መልካም ውጤትም ያመጣል ነው ያሉት፡፡

ምክክር የጋራ ችግርን ወደ ጋራ ሃሳብ ለማምጣትና ለተግዳሮቶች የጋራ መፍትሔ በመስጠት በሰላምና በአንድነትን ለመኖር ትልቅ ጥቅም አለው የሚሉት ምሁሩ፤ የጋራ መፍትሔ ለማምጣትም በኢትዮጵያ ምክክር እየተደረገ ነው ሲሉ ይናገራሉ፡፡

ሀገራዊ መግባባትን ለማምጣት ምሁራንና መምህራን ልዩነትን ያመጡ ነገሮች ምንድናቸው ብለው ሰፊ ጥናት የማድረግ፣ ልዩነቶች ሰፍተው ችግሮች እንዳይባባሱ መፍትሔ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው ያሉት አቶ መለሰ፤ ምሁራን ትውልድን በስነ- ምግባር በማነፅ፤ ማህበረሰብን በመልካምነት በማገልገልና ምርምር በመስራት ምክክሩን እውን የማድረግ ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን ነው የገለጹት፡፡

የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የዋና ዳሬክተር ጽህፈት ቤት ኃላፊ መለሰ አምሽጎ በበኩላቸው፤ ኮሚሽኑ እየሰራ ያለው ስራ የኢትዮጵያን አንድነት ለማምጣት ተስፋ የሚሰጥ ነው፡፡ ሀገራዊ ምክክሩ ተጠናክሮ ከቀጠለ የቀድሞው የህዝብ አንድነት ተመልሶ ይመጣል፤ ባህልንና ሃይማኖትን አክብረን ከሄድን ኢትዮጵያዊ አንድነታችንን ማምጣት እንችላለን፤ አንድነትን ለማምጣት እየተደረገ ያለው ምክክር የሚበረታታና መልካም ውጤት ለማግኘት ተስፋ የሚጭር ነው ይላሉ፡፡

ምክክር ኮሚሽኑ እየሰራ ያለው ስራ ባህልን ከባህል፤ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር አስታርቆ ዘላቂ ሰላምን ማምጣት የሚያስችል መሆኑን ገልጸው፤ይህን ከማሳካት አኳያ ምሁራን ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፤ ሀገሪቱ እየገጠማት ያሉ ችግሮችን ፈትቶ አንድነትን ለማምጣት ተማሪዎች ሀገራዊ ፍቅር እንዲኖራቸው አድርጎ የማስተማር፤ ሕዝብን በአንድነትና በእኩልነት የሚመራ ትውልድ የማፍራት፣ ችግሮችን በምርምር የመለየት፣ ለተለዩ ችግሮች ሁነኛ መፍትሔ የመስጠት ግዴታ አለባቸው ሲሉ ይጠቅሳሉ፡፡

ሀገርን የሚመራ ምሁር ነው፡፡ ሀገርን የሚመራ ምሁር የሚወጣው ከዩኒቨርሲቲ ነው፡፡ ከዚህ መነሻነት የዩኒቨርሲቲ ምሁራን ተማሪዎች ሀገር የሚወዱ ጥሩ ዜጋ ሆነው እንዲወጡ የማድረግ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል ነው ያሉት፡፡

በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን መወያየት፣ መመካከር፣ ሀሳብ መለዋወጥና የጋራ መግባባት ላይ መድረስ አስፈላጊ ነው፡፡ የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስም የምክክር ኮሚሽኑ እየሰራ ያለው ስራ የሚበረታታ ነው ሲሉ የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ መምህር ፈሪያ ሀሰን (ዶ/ር) ይናገራሉ፡፡

ዜጎች በፍቅርና በአንድነት እንዲኖሩ ለማድረግ የምሁራን ሚና ከፍተኛ ነው፤ እኛ ምሁራን ለግጭት የዳረጉንን አለመግባባቶች በመለየት ለችግሮቹ መፍትሔ የመስጠት ኃላፊነት አለብን፤ ይህን ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል ሲሉ ነው የገለጹት፡፡

ሀገራዊ አንድነትን ለማምጣት ግጭት ያለባቸውን ክልሎች በምክክሩ የማካተትና የማሳተፍ ስራ ሊሰራ ይገባል፤ ሁሉን ያሳተፈ ምክክር በማድረግ ሀገርን ወደ አንድነት የማምጣት ስራ መስራት አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

ሀገራዊ መግባባትን ለማምጣት ምሁራን ተማሪዎችን የማስተማር፣ የሀሳብና የልምድ ለውውጥ ማድረግ ሚናቸውን የመጫወት፣ የሃይማኖት አባቶች ምዕመናንን የማስተማር እንዲሁም ከብሔር ብሔር ብሔረሰቦች የተወጣጡ ማህበረሰቦችን ስለሰላም በማሰልጠን በአካባቢያቸው የሚገኙትን ሰዎች እንዲያስተምሩ የማድረግ ስራ ልንሰራ ይገባል ሲሉ ነው ያመለከቱት፡፡

ሀገራዊ ምክክሮችን በማድረግ አዲስ ያደገና የተለወጠ ሥርዓት ባለቤት ለመሆንና በዜጎች መካከል የተሻለ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲኖር ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር፤ እንዲሁም ግጭቶችን በዘላቂነት ለመፍታትና ውይይትን ባህል ያደረገ ችግር አፈታት እንዲዳብር ምሁራን ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡ ይህን ሚናቸውን ከተወጡም የሚፈለገውን ዘላቂ ሰላምና ልማት ማምጣት ቀላል እንደሚሆን ብዙዎች ይስማማሉ፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## በኅብረ ብሔራዊነት የደመቀች ጠንካራ ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ!

ኢትዮጵያ አንድም ብዙም መገለጫ አላት፤ ኢትዮጵያውያንም እንዲሁ በአንድ የወል መጠሪያ ተሰይመው፤ በብዝሃነት ሕብረ ውበት አጊጠው፤ ብዙም አንድም ሆነው የሚገለጥ ማንነት ባለቤት ናቸው። ትናንት በአንድነታቸው ውስጥ አጠንክረው ያነጹት ኢትዮጵያዊነት፤ ዛሬም በብዝኃነታቸው ቀለም አድምቀው የከተቡት የሕብረብሔራዊነት ሰንደቅ አላቸው።

አበው "ድር ሲያብር አንበሳ ያስር" እንዲሉ፤ የበዛው ማንነታቸው የልዩነት ምንጭ ሳይሆን የመተባበራቸው ኅብራዊ ውበት ሆኖ፤ የአብሮነታቸው ደማቅ ግን እንዳይነጣጠሉ አስተሳስሮ የያዛቸው የብዝኃ አንድነታቸውን ገመድ ፈጥሮ ከትናንት እስከ ዛሬ አዝልቋቸዋል። ከዛሬ ባለፈን ነጋቸውን ለመሥራት በሚያስችላቸው ልክ በኅብር እንዲቆሙ ምክንያት ሆኗቸዋል።

ወርሃ ሕዳር ደግሞ፣ የአንድነታቸው ብቻ ሳይሆን የብዝኃነታቸው ዓርማ ደምቆ የታየበት፣ የውል ሰነድ የተከተበበትም ነው። በተለይ ከኢፌዴሪ ሕገመንግሥት መጽደቅ ጋር በተያያዘ፤ የኢትዮጵያ መልከ ብዙነት፤ የኢትዮጵያውያንም ኅብረ-ብሔራዊነት ከእውነትነት ባሻገር ላለው ቅቡልነት መሠረት መጣል ተችሏል።

የትናንት አብሮነታቸው በጽኑ መሠረት ላይ እንዲኖር፤ የዛሬ እውነታቸው እንዲገለጥ፤ የነገ ሕልምና ተስፋዎቻቸው በወል እሳቤያቸው ላይ ይገነባና ይመራ ዘንድ እርሾ ሆኖም እያገለገለ ይገኛል። በዚህም ሕዳር 29ኝ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ብሎ በመሰየም፤ ኅብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያን ለመግለጥ የተሄደበት አግባብም ነበር።

ይሁን እንጂ ይሄ ሕገ መንግሥታዊ ማረጋገጫ ያገኘው የኅብረ-ብሔራዊ አንድነታቸው ጉዳይ ከወቅቱ የፖለቲካ ሥሪት አኳያ ባልተገባ መልኩ እንዲገለጥ ሆኖ ቆይቷል። ምክንያቱም፣ ሁነትና ሂደቱ ከአብሮነት ይልቅ ልዩነት ላይ፤ ከመተባበር ይልቅ መነጣጠል ላይ፤ ከሚያሰባስቡ ትርክትና እሴቶች ይልቅ በሚከፋፍሉ አጀንዳዎች ላይ፤... ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራ ቆይቶ ነበርና።

ይሄም ከወል ማንነት በላይ ተናጠላዊ ማንነት ገዝፎ፣ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት እስኪረሱ በደረሰ መልኩ እንዲፈረጁ ጥረት ተደርጓል። በተወሰነ ደረጃም ባይሆን ጥረቱ ፍሬ ለመቋጠር ደርሶም ነበር። ለዚህም ነው በተለይ በለውጡ ማግስት ችግሮች፣ መፈናቀልና አለመረጋጋቶች፣ እልፍ ሲልም ጦርነቶች እዚህም እዚያም መታየታቸው።

የዚህ ችግሩ ታዲያ፣ ኢትዮጵያዊነት እንዲጠላ፤ የብሔር ማንነት ከፍ ብሎ እንዲወጣ እና በብሔር ጥላ ስር የሀገርነት እሳቤ እንዲያቆጠቁጥ በመደረጉ ነው። በማንነት መብት ስም የመነጣጠል ትርክት ሥር እንዲሰድ በመሠራቱም ነው። ከኢትዮጵያ ይልቅ ለክልል፣ ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ለተናጠላዊ ማንነት ከፍ ያለ ሥፍራ እንዲሰጥ በመሰበኩም ነበር።

ሆኖም ይሄ የተሳሳተ አካሄድ፣ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን የትናንት የበዛ የጋራ ታሪክ፣ መንገድና ገድላቸውን እንዳያውቁት፤ በኢትዮጵያ በሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ሚናና ድርሻ እንዳይገነዘቡት፤ እንደ ሀገር የወደፊትን ተልሞ እና ተባብሮ የመሥራትን አቅምነት ሳይሆን፣ ለብቻ በመቆም ውስጥ ከፍ ያለ ጥቅም የመገኘቱን አማላይ ግን ከእውነት የተፋታ ትርክት ደጋግመው እንዲያደምጡ በማድረግ ውስጥ የተቃኘ ነበር።

ለዚህም ነው ከ2010ሩ ሀገራዊ ለውጥ ማግስት ታዲያ ይሄንን የተሳሳተ ትርክት የማረም፣ እውነተኛውን እና ለኢትዮጵያም፣ ለኢትዮጵያውያንም የሚጠቅመውን የወል መንገድ፤ በኅብር የደመቀውን አብሮነት፤ ትክክለኛውን ኅብረ-ብሔራዊ ዴሞክራሲ በተግባር መግለጥ ትልቅ ትኩረት የተሰጠው።

ከተናጠል ይልቅ በጋራ መቆም ያለውን የላቀ አቅም በኢትዮጵያ የሺህ ዓመታት ጉዞ ውስጥ በጋራ ሆኖ የተሠራውን ሥራ ታላቅነት የመግለጥ ሥራ መጀመሩ፤ ከነጣጣይ ትርክቶች ይልቅ ለአሰባሳቢ ሀገራዊ አብይ ትርክቶች ቦታ መሰጠቱ፤ እውነተኛ የኅብረ-ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ሥርዓቱ እቅኝቱ ኢትዮጵያውያን ማንነታቸውን ከፍ አድርገው ደግሞም ኢትዮጵያዊነታቸውን አልቀው በማይጋጭ ማንነት ውስጥ እንዲገለጡ በሚያደርግ መልኩ እየተተገበረና ውጤት እያስመዘገበ መምጣቱ፤... የትናንት ስህተትን ለማረም እንዲቻል ነው።

ይሄ ጅምር የትናንት ስህተትን ማረም ላይ ብቻ ያተኮረም አይደለም። የዛሬን ተጨባጭ ሃቅና እውነት በመግለጥ፤ ከትናንት ጉዳይ አሰላሳይነት (ባለፈ ሁነትና ክስተት ላይ ተቸካይነት) ማላቀቅንም ማዕከል ያደረገ፤ ከትናንት ይልቅ ዛሬ የተሻለ ስለመሆኑ፤ ከዛሬም ደግሞ ነገ በእጅጉ የተሻለ ስለመሆኑ፤ እናም በእጅጉ ለተሻለው ነገ ሲባል ትናንት ላይ ከመቸከል ይልቅ የትናንቱን ረስቶም፣ በይቅርታ ተሻግሮም ለልጆቻቸው መልካም ዕድልን በሚያኖረው ነገ ላይ ማተኮር እንደሚገባም የሚያስገነዝብ ነው።

ይሄ እጅጉን የተሻለው ነገ፣ ለልጆቻችን የተሻለ እድልን የምናቀብልበት ነገ፤ ከትናንት ቁርሾና ንትርክ ነጻ የሚያወጣን ነገ፤ ከመነጠል ይልቅ በኅብር የመቆማችንን ኃያልነት እንድንገነዘብ የሚያደርገን ነገ፤... ዝም ብሎ የሚመጣ አይደለም። ዛሬን መሥራት፤ ዛሬን ዋጋ መክፈል፤ ዛሬን በንጹህ ልብ ሆኖ ቁጭ ብሎ መነጋገር፤ ዛሬን ስለ ትናንት ሳይሆን ስለ መጪው እያሰላሰልን የተሻለ ነገርን የመተለም ልዕልናን ከእኛ ይሻል።

እናም ነገ ይሄን መሰሉ የሰው ልጅ ልዕልና ገንዘባችን እንድናደርግ ይፈልጋል ሲባል፤ ማንነታችንን ይዘን ኢትዮጵያዊነታችንን ከፍ ማድረግ፤ አንድነታችንን አጠንክረን ኅብረ-ብሔራዊነታችንን መግለጥ፤ ታሪካችንን ከተዛባ መስመሩ አውጥተን በትክክለኛና እውነተኛው ትርክት ማነጽና የጋራችን የሆነውን ሃቅ ማኖር፤ ትናንት ልክ ነው ተብሎ በተፈጸመው ችግር ተተብትበን ከመባላት ወጥተን፣ ስለ ልጆቻችን ብሩህ ነገና ዕጣ ፈንታ በወል ሆነን አስበን በወል ሆነን የምንራመድበትን አውድ መሥራት ማለት ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## "ደረሰኝ ሳይቀበሉ ሂሳብዎን አይክፈሉ!"

**አዶኒስ (ከሲኤምሲ)**

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን ደጋግመን በአይናችን እናያቸውና ምንም እንዳልሆኑ አድርገን እንቆጥራቸዋለን። በየገባንበት የንግድ ማዕከል፣ በየመዝናኛ ስፍራው፣ በገበያ ቦታ፣ በየሆቴሉ፣ በየቁርጡ ቤት ... ማሳሰቢያ ይሁኑ የግድግዳ ማስዋቢያ ጥያቄ እስኪፈጥሩብን ድረስ እንዘነጋቸዋለን። ምንም እንዳልሆኑ ምንም እንደማያስከትሉ አድርገን እንለምዳቸዋለን። "ደረሰኝ ሳይቀበሉ ሂሳብዎን አይክፈሉ!" የሚለው መልዕክት በእዚህ እሳቤ ውስጥ ከሚታዩት ትዕዛዝ አዘል ማሳሰቢያዎች መካከል አንዱ ነው።

ማንኛውም ማስታወቂያ በየትኛውም ቦታ ላይ ከተለጠፈ ወይም ከተሰቀለ መልዕክቱ መተግበር አለበት። በማስታወቂያው ግርጌ ላይ የሚቀመጡ የስልክ ቁጥሮችም የራሳቸው ዋጋ አላቸው። ‹‹ያጋጠመህን ችግር በስልክ ቁጥሮቹ ደውልና አሳውቀን። ቅሬታው በትክክልም ጥፋት ሆኖ ከተገኘ አጥፊውን ወይም ሕግ የጣሰውን በሕግ ተጠያቂ እናደርጋለን›› የሚል ውስጠ ምስጢር ያዘለ ይመስለኛል።

በተሰጠው ስልክ ቁጥር የደወለው አካል ባገኘው አገልግሎት ረክቶና ተደስቶ ለማመስገን ከሆነም ሙሉ መረጃውን ይዞ ለተገቢው አካል ተገቢውን ግብረ መልስ ለመስጠት እንጠቀምበታለን የሚል ይመስለኛል። ይህ የሚሆነው ትክክለኛ ያልነውን መንገድ የተከተልን እንደሆነ ነው። ‹‹አሁንስ?›› ካልን የአንዳንድ ማስታወቂያዎችና በግርጌያቸው የሚገኙ ስልክ ቁጥሮች ከጌጥነት ያለፈ ፋይዳ ያላቸው አይመስሉም። ምክንያቱም ስልክ ቁጥሮቹ የቢሮ ናቸው፤ የቢሮ ስራና ሰዓት ደግሞ ይታወቃል። ስለዚህ ማንም ሰራተኛ ወይም ኃላፊ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል ብሎ የሚያስብ ሰው አይኖርም። ምክንያቱም የብዙ ነገር አገልግሎት ልውውጥ የሚኖረው ከስራ ሰዓት ውጪ በበዓላት ቀንና በምሽት ጭምር በመሆኑ የቢሮ ስልክ የሚያነሳና ቅሬታውንም ሆነ ምስጋናውን የሚቀበል አለ?

"ደረሰኝ ሳይቀበሉ ሂሳብዎን አይክፈሉ!" የሚለውን መልዕክት የምናገኘው ከዋናው ከተማ እስከ ገጠር ድረስ ነው። በእያንዳንዱ ንግድ ቤት ውስጥ በጉልህ ተጽፎ ይነበባል። ኧረ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከአንድ በላይ ማስታወቂያ በየግድግዳው ሁሉ ተለጥፎ ይታያል። ሆኖም ግን ማስታወቂያው ከማስታወቂያነት ባለፈ ሂሳቡ ተከፍሎም ደረሰኙን ማግኘት እጅግ ከባድ የሚሆንበት ሁኔታ አለ። ይሄ አገልግሎት ባገኘውም አገልግሎት በሰጠውም አካል ክፍተት ወይም ድክመት የሚመነጭ ነው።

አንዳንድ ሰው ላገኘው አገልግሎት ክፍያ ለመፈጸም "ሂሳብ አምጡልኝ" ብሎ ሲጠይቅ አስተናጋጁ ደረሰኙን ይዞ ብቅ ከማለት ይልቅ እጁን ወደ ኋላ አድርጎ የሂሳቡን መጠን ይናገራል። "ደረሰኝ አምጣ እንጂ" የሚል ጎበዝ የገጠመው እንደሆነ ፈጠን ብሎ፣ ‹‹መብራት ጠፍቶ ነው›› ወይም ‹‹ደረሰኝ አትጠይቁን›› የሚሉ ገፍታሪ መልሶችን ይደረድራል። ኧረ "መብራት ሲመጣ ኑ" የሚሉም አልጠፉም። "ዛሬ እንኳን እንስራበት! ላሽ በል" የሚልም አራዳ መሳይ አጭበርባሪ ያጋጥማል። የተገልጋዩን ሂሳብ ከኪሱ አስወጥቶ የመንግሥትን ድርሻ ወደ ካዝናው የሚያደርግ ሰው አራዳ መሆኑ ነው? አንዳንዱ ደግሞ ለማያውቀው (ድንገት ለተከሰተ ደንበኛ) ብቻ ነው ደረሰኝ የሚቆርጠው። ሌሎች ‹‹ቤተሰብ›› ናቸው። በዚህ ሰበብ የመንግሥት ገቢ የግለሰቦችን ኪስ ያሞቃል። እዚህ ላይ ወንጀለኛው ሁለቱም አካል መሆኑን ልብ ማለት ይገባል።

ዛሬ ላይ ደረሰኝ ስጡኝ አትስጡኝ ለሚለው ንትርክ የዳረገን ለታክስና ግብር ያለው የተዛባ አመለካከት ነው። "ያለደረሰኝ አትሽጡ፣ ትክክለኛ ገቢያችሁን አሳውቁ፣ ኮንትሮባንድ ንግድ አቁሙ፤ወደ ቫት ሥርዓት ግቡ፣ ንግድ ፈቃድ የሌላችሁ ንግድ ፍቃድ አውጡ፣ ደረሰኝ መቁረጥ ደረጃ የደረሱ ነጋዴዎች ደረሰኝ አስፈቅደው ያሳትሙ፣ በአጠቃላይ የንግድና የግብይት ሥርዓቱ ህጋዊ መስመር የተከተለ ይሁን" የሚል ጠበቅ ያለ እንቅስቃሴ በመንግሥት በኩል በመጀመሩ ነው። ይሁን እንጂ ሕገወጥነት እንዲጠፋ የማይፈልጉ አካላት ህብረተሰቡን የሚያውኩና ለአመጽ የሚቀሰቅሱ ወሬዎችን አስቀድመው ይነዛሉ። ወከባ ይፈጥራሉ፤ግርግር ያስነሳሉ።

ሰሞኑን በመርካቶ አካባቢ ያየነው ግርምትን ያጫረብን ጉዳይ ነው። በእርግጥ ሁሉንም የንግዱ ማህበረሰብ አጭበርባሪ፣ አወናባጅ፣ ሕገወጥ ነው ብሎ መደምደም አይቻልም። በጣም ምስጉን የሆኑ፣ ሕግና ሥርዓት ተከትለው የሚሰሩ በሥነምግባር የሚታወቁ ብዙ ስመጥሩ ነጋዴዎች አሉ። አንቱ የተባሉና ከዘመን ዘመን ከነስምና ክብራቸው የዘለቁ አሉ። በሀቀኛ ግብር ከፋይነት የተመሰከረላቸው በጠቅላይ ሚኒስትሩ እውቅና እስከማግኘት የደረሱ ‹‹የቄሳርን ለቄሳር የእግዜሩን ለእግዜር›› ብለው በሀቅ የሚሰሩ ብዙ የንግድ ማህበረሰቦች አሉ። እነዚህን ጨምሮ የንግዱ ማህበረሰብ ብሎ በጅምላ መውቀስ አይቻልም። እነዚህን ሀቀኛ የሕዝብ አገልጋዮችን ሽፋን አድርገው የሚሰሩትን ግን መቼም ቢሆን መውቀስና ማውገዝ ይገባል።

"ሕጋዊ ሥርዓት ይዘርጋ፣ ሰው የልፋቱን፣ የላቡን ያግኝ" ሲባል "ሱቅ ሊዘጉ ነው፤ንብረት ሊወርሱ ነው" የሚል ሽብር መንዛት ተገቢነት የለውም። ሱቅን መዝጋትና መሸሸም መፍትሄ አያመጣም። ሀቀኛ ነጋዴ ማንም ይምጣ ምንም ይምጣ ለሚጠየቀው ሁሉ የሚሰጠው መልስ በልበ ሙሉነት በተሟላ መረጃና ማስረጃ መሆን ይኖርበታል። ለዚህም በሩን ክፍት ማድረግ ነው የሚጠበቅበት። ከተቆጣጣሪ አካል ጋር ድርድር ፣ ንብረት ማሸሽ የመሳሰሉት ውስጥ መግባት የትም አያደርስም። ምክንያቱም በየትኛውም ዓለም ለሀገር ዕድገት አንዱ የገቢ ምንጭ ታክስ፣ ግብር፣ ቫት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

አሁን ባለው ሁኔታ ምንም ማጭበርበር የሌለበት ነው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር የሚቻለው የመንግስት ሰራተኛው የሚከፍለውን ታክስ ነው። የመንግስት ሰራተኛው የሚጠበቅበትን ታክስ ገቢ የሚያደርገው ከዋናው ደመወዙ ፔሮል ላይ ተቆርጦ ነው፤ ስለዚህ በማንም ሰው እጅ ላይ የሚገባ ገንዘብ ባለመኖሩ ሳይቆረጥ የሚቀር ወይም የሚጭበረበር ታክስ አይኖርም። ለዚህም ነው የመንግሥት ሠራተኛው ሳያጭበረብር ታክስ ይከፍላል የምንለው።

በከተማዋ በርካታ ነጋዴዎች በግብር ከፋይነት ተመዝግበው ደረሰኝ የማይሰጡ በመሆናቸው እና ችግሩም በጣም እየሰፋ በመሆኑ ወጥነት ባለው መንገድ ሕጉን እንዲያከብሩ እና ወደ ሥርዓት እንዲገቡ የማድረግ እንቅስቃሴ በከተማ አስተዳደሩ ተጀምሯል። ይህ ይበል የሚያሰኝ ጅምር ነው። በነገራችን ላይ አንድን ጉዳይ ሕግና ሥርዓት ለማስያዝ ሲሰራ፣ የችግሩ አስኳል የሚገኘው በሌላ ቦታ ሌላ አካል ላይ ሊሆን እንደሚችል መገመትና ሰንኮፉን ለይቶ ለማውጣት መስራት ይገባል። አስመጪዎችና ጅምላ አከፋፋዮች አካባቢ ያለውንም በነካ እጃችሁ ማለት ያስፈልጋል። በቸርቻሪነት ሥራ ላይ ያሉትንም አለብን የሚሉትን ችግር በደንበ ማድመጥና መፍትሄ መስጠት ይገባል። ይሄ ሲሆን ነው ፍትሐዊ ውድድር የሚሰፍነው፤ ሕግና ሥርዓት የሚከበረው፤ደረሰኝ ስጠኝ ከሚለው ሙግትም የሚወጣው።

ሕግና ሥርዓት በከተማችን ብሎም በሀገራችን ሲሰፍን ‹‹ደረሰኝ ሳይቀበሉ ሂሳብዎን አይክፈሉ›› የሚለው ማሳሰቢያ መሳይ ማስታወቂያ ከጌጥነት ያለፈ ሚና ይኖረዋል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ቀይ ባሕርና ዓባይ ለኢትዮጵያ ምን እና ምን ናቸው

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)

ላለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ፍጆታ በመሆን በቀዳሚነት የሚጠቀሰው የውሀ ፖለቲካ ነው ብል ተሳሳትክ አትሉኝም። በርካታ የታሪክ ምሁራንም ይሄን እውነት በመደገፍ የተለያዩ ሀሳቦችን ሲያነሱ ቆይተዋል። አንዳንዶች እውነቱን ሲቀበሉ የተቀሩት ደግሞ በራስ ወዳድነት የበላይነታቸውን ሊያሳዩ ሲሞክሩ ታዝበናቸዋል። በቀይ ባሕርና በዓባይ ውሀ ላይ የሚነሳው ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ የይገባኛል ንትርክ ከትናንት ወደዛሬ የመጣ ወቅታዊ የፖለቲካ አጀንዳ በመሆን ብዙዎች በአንክሮ እየተከታተሉት ይገኛሉ።

ይሄን ጉዳይ በአንክሮ ከሚከታተሉ ሀገራት መሀል ኢትዮጵያ ቀዳሚዋ ስትሆን ዓለም አቀፉን ስምምነት በተከተለ የአብሮ መስራት አቋም ከጎረቤት ሀገራት ጋር በትብብር ለመስራት ፍቃደኝነቷን በመግለጽ ላይ ትገኛለች። ቀይ ባሕርም ሆነ ዓባይ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ይዞታ እንደሆኑ በታሪክ አጥኚዎች የተረጋገጠ ቢሆንም እውነታውን የካዱ ሀገራት ግን ራስን ብቻ ለመጥቀም በተነሳሳ ፍላጎት የአብሮ እንስራ ጥያቄን አሻፈረኝ ብለዋል።

ቀይ ባሕር እና ዓባይ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ታሪካዊ ተዛምዶ በተመለከተ መጽሀፍ በመጻፍና ጥናት በማድረግ እውነታውን ከሚናገሩት መሀል የታሪክ ምሁሩ አቶ ዳኛው ተስፋው አንዱ ናቸው። ቀይ ባሕር በጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ስልጣኔ ላይ ሰፊ ድርሻ ያለው፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን በመምራት በዓለም ላይ ካሉ በጣት ከሚቆጠሩ ስልጡን ሀገራት መሀል ወሳኝ በመሆን የሚጠራ መሆኑን አስታውሰው፤ አሁን ባለው ሁኔታ የባሕር በር ጥያቄ ተገቢ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ከዚህ ጋር አያይዘው ኢትዮጵያ ካላት የኢኮኖሚ ግዝፈትና በቀጣናው ካላት ተጽዕኖ ፈጣሪነት አኳያ የባሕር በር እንደወደብ ሳይሆን እንደሕልውና የሚታይ ጉዳይ ነው ሲሉ ወሳኝ እውነታን ገልፀዋል። አሁን ላይ ነገሮች ቀልድና ዋጋ የሌላቸው ሊመስሉ ይችላሉ። ጥቅማቸው ምን ያክል እንደሆነ ነገ ላይ ነው የሚታወቀው። የባሕር በር ለሚመጣው ሀገራዊ እቅድና ትልም ከዛሬ ይልቅ ለነገ ወሳኝ መሆኑን አመልክተዋል።

ይሄ የታሪክ ምሁሩ ንግግር በቀይ ባሕርና በዓባይ ላይ የጀመርነው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በፍላጎትና በይገባናል የሚያበቃ ሳይሆን የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ እንደሆነ የሚጠቁም ነው። ሰፊና ግዙፍ በሆነ ሀገርና ሕዝብ መሀል በእርግጥም ሚዛን ደፊ እውነታ ነው። የታሪክ ምሁሩ ሰፊ የጥናት ዳሰሳ እንደሚያሳየው ከሆነ ሀገር እየሰፋ፣ ሕዝብ እየበዛ ነው የሚሄደው።

በዚህ ስፋትና ብዛት መሀል ደግሞ የፍላጎት ጥያቄ ይመጣል። ፍላጎትን ለማሟላት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው በኢምፖርትና ኤክስፖርት በበቂ ሁኔታ መሳለጥ ያስፈልገዋል። የኢኮኖሚው ሁኔታ እንዲቀላጠፍ ራስ ገዝ የሆነ የወደብ አስፈላጊነት ወሳኝ ሆኖ ይመጣል። ቀይ ባሕር ለኢትዮጵያ ወደብ ብቻ ሳይሆን የሕልውና ጉዳይም ጭምር ነው ስንል ለዚህ ነው።

በአሁኑ ሰዓት የዓለም ትኩረት ውሀ ላይ ነው። እነ ነዳጅ ወርቅና ውድ ማዕድናት የውሀን ያክል ዋጋ የማያወጡበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ይሄ ዘመን ‹የውሀ ገንቦ› በሚል በቁልምጫ ለምትጠራው ሀገራችን ከመቼውም ጊዜ በላይ ምቹ አጋጣሚን የሚፈጥር ነው። በአንድ ዓላማ ያሉንን የውሀ ሀብቶ ቻችንን በተገቢው መንገድ ለተገቢው ዓላማ መጠቀም ከቻልን በኢኮኖሚው ሆነ በፖለቲካው የበላይነትን ከማምጣት ባለፈ የደህንነት ዋስትናም እናገኛለን። ይሄ ሳይሆን ቀርቶ በያዝ ለቀቅ ወይም ደግሞ ደጋፊና ተቺ በመሆን ጎራ የምንለይ ከሆነ በረከቶቻችን ጣጣ ይዘውብን የማይመጡበት ምንም ምክንያት የለም።

ላነሳነው ጥያቄና ወደፊትም ለምናነሳው ህዝባዊ ጥያቄ የጋራ አቋም መያዝ እንዲህ ባለው ጉዳይ ላይ ወሳኝነት አለው። ሕዝባዊ አንድነት ያለውን ፋይዳ በተለያየ አጋጣሚ እናስተውላለን። በሀገር ደረጃ የተመዘገቡ ደማቅ ድሎች በአንድ ዓላማ ለአንድ የቆምንባቸው ናቸው። በዓባይ ግድብ ላይ እያሳየነው ያለው የበላይነት የአብሮ መጽናት ሕዝባዊ ዓላማ እንደሆነ ግልጽ ነው። በቀይ ባሕር ላይ የነበረንን ይዞታ በአዲሱ ትውልድ የይገባኛል ጥያቄ መልሰን ወደነበርንበት የከፍታ ዘመን መመለስ የጋራ የቤት ስራችን ነው።

ሀያላኑን ጨምሮ ብዙ ሀገራት በውሀ ፖለቲካ ላይ አነጣጥረዋል። በአሁኑ ሰዓት ዓለም ከተሳሰረችበትና ወደ አንድ አቋም ከመጣችበት ጉዳይ አንዱ የውሀ ፖለቲካ ነው። ቀይ ባሕር፣ ስዊዝ ካናል፣ ኤደን ባህረ ሰላጤ የንግድ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ የሌላም ሌላ ፍላጎት ማስፈጸሚያ ኮሪደር ናቸው። ብዙዎች በበላይነት ሊቀራመቱት በእኔ እበልጥ እኔ ሽኩቻ ውስጥ ከገቡ ሰንበትበት ብለዋል።

እዛ አካባቢ የሚሆን የትኛውም ድርጊት ዓለም አቀፍ ትኩረትን ለማግኘት ደቂቃ አይፈጅበትም። ቦታው አህጉራት ከአህጉራት፣ አውሮፓ ከአፍሪካ እና ከኢሲያ ጋር ሌሎችም እንደዚሁ አንዱ ከአንዱ ጋር የንግድ ልውውጥ የሚያደርጉበት ስለሆነ ትኩሳቱ የጋራ ነው። ለአብነት ብንጠቅስ በ1960 ገደማ በእስራኤልና በአረቦች መካከል በተፈጠረው ግጭት ብዙሀኑን የነካ የኢኮኖሚ ቀውስ ተፈጥሮ ነበር።

እንደታሪክ አዋቂው ዳኛው ተስፋው ገለጻ፤ ዓባይ አልፎ ከሚሄድባቸው ሀገራት ተጨማሪ ለመዳረሻነት የሚፈልጉት ብዙ ሀገሮች እንዳሉ ሰምተናል። ሳውዲ አረቢያ በግብጽ በኩል ተንጠራርታ መዳረሻዋ ልታደርገው ሙከራ እንዳደረገች፣ የሰሜን አፍሪካ ሀገራት እንደዚሁ መዳረሻቸው ሊያደርጉት ብርቱ ፍላጎት አላቸው።

ግብጽ በተሳሳተ ስምምነት በዓባይ ውሀ ላይ ፈላጭ ቆራጭ በመሆን ብዙ ዘመናትን ተጉዛለች። ለቀረቧት ወዳጅ ሀገራት እንደእርጎ እንኳን ደህና መጣችሁ ስትል ከውሀዋ ቀድታ መስጠት ልማዷ ነው። በታሪክ የሚታወሰው ከእስራኤል ጋር በነበራት ጉርብትና በመሪዋ በኩል ‹ዓባይን ውሀ አብረን እንጠጣለን› ስትል የተናገረችው ነው። ይሄ የድፍረት ንግግሯ በዓባይ ላይ ያላትን የበላይነት በመሻር ዓባይ ወደትውልድ ሀገሩ በመመለስ ጥሞኞችን ሊያረሰርስ ግድብ ሆኖ መጥቷል።

እንደኢትዮጵያ ያሉ አንድና ሁለት በአብሮ መስራት መርህ የሚያምኑ ሀገራት ቢኖሩ ዓባይና ቀይ ባሕር ይሄን ያክል መከራከሪያ ባልሆኑ ነበር። የዓባይ ውሀ ካየነው ብዙ ነገሩ ከኢትዮጵያ ነው፣ ቀይ ባሕርም በቅርብ ርቀት ላይ ያለ ከታሪክ የተዋረሰ ግዛቷ ነው። እንደዛም ሆኖ ለብቻዬ ልጠቀም የሚል የላትም። ለየት የሚያደርገውና እኛንና ጉረቤት ሀገራችንን ስለፍትህ ላይና ታች ያስቀመጠው 12 የሚሆኑ ወንዞቻችን ድንበር ተሻጋሪ ሆነው ሌሎች የመኖር ዋስትና መሆናቸው ነው።

እነዚህ ሀገራት ዓባይ ብለን ግብጽ እንደምንለው በእኛ የተፈጥሮ ጸጋ ያተረፉ፣ የከበሩ ሀገራት ናቸው። የሚገርመው ደግሞ ውሀችንን ጠጥተው ያደጉና በውሃችን ሀገር የሆኑ ሀገራት ዛሬ ላይ ስለቀይ ባሕር ጥያቄ ስናነሳ መከፋታቸው ነው። አስራ ሁለት ወንዞቻችን ድንበር አልፈው ወደጎረቤት ሀገራት ሲሄዱ እኛ ከሌሎች ያገኘነው ምንም አልነበረም። በተቃራኒው ግብጽ ዓባይን በተሳሳተ ትርክት የራሴ ነው ብላ እንዳመነችው እነዚህም ሀገራት ስለወንዞቻችን ምስጋናን ከመቸር ይልቅ ስለወንዞቻችን ጥርጣሬን ነው ያስቀደሙት። ወደብ ያስፈልገናል፣ ዓባይን ገድበን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት መውጣት እንፈልጋለን ስንል እንኳን ይሁንታን አላሳዩም።

ባለን ታሪካዊና ወቅታዊ ግዝፈት የቀይ ባሕርም ሆነ የዓባይ ጉዳይ በዋናነት እኛን የሚታከክ ነው። ችግሩም መፍትሄውም ምስራቅ አፍሪካን በተለይም እኛን ነክቶ የሚያልፍ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ከሌሎች ሀገራት ጋር ባለን ንጽጽር ተጽዕኖ ፈጣሪ ሆነን የመታየት እድላችን የገዘፈ ነው። በሕዝብ ቁጥር፣ በኢኮኖሚ ግስጋሴ፣ በቀጣናው ባለን ተደማጭነት በውሀው ፖለቲካ ላይ ፊተኝነትን እንድናገኝ አድር ጎናል። የታሪክ ተመራማሪው ይሄን ጉዳይ ሲገልጹ ‹ባላት ወቅታዊ ቁመና ኢትዮጵያ በዓባይና በቀይ ባሕር ላይ እንደተጽዕኖ ፈጣሪና እንደስጋት የምትታይ ናት› ብለው ነው።

> **ሶማሊያ በዋቢ ሸበሌና በገናሌ ወንዞቻችን ሕልውናዋን ስታቆም ስምን አላልንም። ግብጽና ሱዳን በዓባይ ውሀ ስልጣኔን ሲያቆሙ ደስ አለን እንጂ አልተቃወምንም። ተራችን ደርሶ በሀብታችን ስመጠቀም ስንሞክር መተባበር እንጂ መቃወም ትዝብት ላይ የሚጥል ነው። እንዲህ ያሉ የብቻ ፍላጎቶች ኢትዮጵያን ሳይሆን ራሳቸውን የሚጎዳ እንደሆነም የታሪክ አጥኚዎች ይገልጻሉ**

የዚህ ዘመን ‹ሰማያዊ ወርቅ› በሚል ስም የሚጠራው ውሀ ባላቂ የተፈጥሮ ሀብት ስር ብዙዎች አትኩሮት የሚያደርጉበት ከሆነ ሰነባብቷል። ለዚህ እንደዋነኛ ምክንያት በመሆን የሚነሳው ደግሞ ተተኪ አለመሆኑ፣ ለመገኘት ብዙ መስዋዕት የሚጠይቅ መሆኑ፣ ለሕይወት እጅግ ወሳኝ መሆኑ እና ውሱን የተፈጥሮ ሀብት በመሆኑ ነው። ውሀ ያለው ሀገር ነዳጅ ካለው ሀገር በበለጠ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቁመና ላይ ለመገኘት ቅርብ እንደሆነ የመስኩ ባለሙያዎች ይመሰክራሉ።

በወቅቱ የነበሩ ወሳኝ ጉዳዮች ለአንደኛውና ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት መከሰት ምክንያት ሆነዋል። እጅግ ወሳኝና አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ ሶስተኛው የዓለም ጦርነት በውሀ እንደሚነሳ የሚተነብዩ የታሪክ ሰዎች እየተፈጠሩ ነው። ጦርነት በውሀ ይነሳል ብሎ የገመተ ማን ነበር? ከምድራችን 71 በመቶ ውሀ እንደሆነ ከዚህ ውስጥ ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆነው 3.5 መሆኑ ጉዳዩን ትኩረት እንዲያገኝ አድርጎታል። እንግዲህ ዓለም ግብግብ የያዘው 5 ፐርሰንት ባልሞላ በዚህ ውስን የውሀ ድርሻ ላይ ነው።

እንደሀገር ተፈጥሮ በብዙ የባረከችን ሕዝቦች ነን። በተለይ ውስን በሆነው የውሀ ሀብት ላይ በርካታ ጸጋዎች ተችሮናል። ከጸጋዎቻችን መሀል ደግሞ አባይና ቀይ ባሕር ይገኙበታል። የታሪክ ምሁሩ ዳኛው ተስፋው ‹ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር እና የዓባይ ባለይዞታ ናት› ሲሉ ጠበቅ ያለ መልእክታቸውን በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ አስፍረዋል። ከዚህ የባለታሪክ ሀሳብ ተነስተን እያደረግነው ያለው የሕዳሴ ግድብም ሆነ የወደብ ጥያቄ ሕጋዊና በራስ ተፈጥሮ ላይ እንደመጠቀም የሚቆጠር መሆኑን እንረዳለን።

አሁን ባለው የውሀ ፖለቲካ ቀይ ባሕርም ሆነ ዓባይ ከፍታዊ ተጠቃሚነት ባለፈ እንደህልውና ሊታዩ የሚችሉ ናቸው ሲሉ የታሪክ ምሁሩ ያሳስባሉ። ማስተንፈሻ ኮሪደር እንፈልጋለን ስንል ለአሁናዊ ጉዳይ ሳይሆን ከቀጣዩ የሕዝብ ቁጥርና የትውልድ ፍላጎት አንጻር አብሮ ሊታይ የሚገባው ነው ይላሉ። የወደብ ጉዳይ ከኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ጎን ለጎን የሉአላዊነት እና የደህንነት ጉዳይም ጭምር ነው። የታሪክ ተመራማሪው ዳኛው አስፋው ይሄን እውነታ ‹ቀይ ባሕርን በሸሸነው ቁጥር የሀገራችን ሕልውና እየተቃወሰ ይሄዳል› ሲሉ ነው የገለጹት። ይሄ እውነታ እንደ መልዕክት ለሁላችንም አንቂ ደወል ሆኖ የሚቀመጥ የቤት ስራችን ነው።

በንግድ ልውውጥ ሂደት ወቅት ርካሽ በመሆን ተመራጩ የባሕር ላይ ማጓጓዣ ነው። ለሸቀጦች፣ ለምርቶች፣ ለጥሬ ሀብቶች ለሌሎችም የኢምፖርትና የኤክስፖርት ንግድ የባሕር ትራንስፖርት ወሳኝ በመሆን ጥቅም ላይ ይውላል። ለዚህ እንደጥሩ የሚነሳው ቀይ ባሕር ነው። በኢሲያ፣ በአፍሪካና በአውሮፓ መካከል በመኖሩ እንደማዕከል በመሆን ከብዙዎች ለብዙዎች ግልጋሎት በመስጠት ቀዳሚ ነው።

የኢትዮጵያ ነባር አቋም ሕብረት ፈጥረን በጋራ እንልማ የሚል ነው። ሰጥቶ የመቀበል መርህ በጋራ ተጠቃሚነት የሚያምን የጋርዮሽ መስተጋብርን የሚያጎለብት ነው። ቀይ ባሕር ካለው ግዝፈትና እየሰጠ ካለው ብዙ ጥቅም በአብሮ መስራት ካልሆነ በብቻ ፍላጎት የሚሆን አይደለም። ሶማሊያ በዋቢ ሸበሌና በገናሌ ወንዞቻችን ሕልውናዋን ስታቆም ለምን አላልንም። ግብጽና ሱዳን በዓባይ ውሀ ስልጣኔን ሲያቆሙ ደስ አለን እንጂ አልተቃወምንም። ተራችን ደርሶ በሀብታችን ለመጠቀም ስንሞክር መተባበር እንጂ መቃወም ትዝብት ላይ የሚጥል ነው። እንዲህ ያሉ የብቻ ፍላጎቶች ኢትዮጵያን ሳይሆን ራሳቸውን የሚጎዳ እንደሆነም የታሪክ አጥኚዎች ይገልጻሉ። ስለዚህ ለእኔ እና ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለኛ በሚል በመተባበር መንፈስ ሀብታችንን ማልማትና በጋራ መጠቀም ይኖርብናል የሚለው የዛሬው መልዕክቴ ነው። አበቃሁ!

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የሕብረተሰቡ ችግር የወለዳቸው የፈጠራ ሥራዎች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በሀገሪቱ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚሰሩ የፈጠራ ሥራዎችን ለሕብረተሰቡ በማቅረብ ባለተሰጥኦዎች እንዲበረታቱ የሚያነሳሱ ሥራዎች በየጊዜው እየተሰሩ ይገኛሉ። የፈጠራ ስራዎቹ በተለያዩ አውደ ርዕዮች እንዲታዩና እንዲወዳደሩ የማድረጉ ሂደት ቀጥሏል። ባለፈው ሳምንትም ከእነዚህ መካከል አንዱ የሆነው ዘጠነኛው ዙር ሀገራዊ የሳይንስና ምህንድስና ቀን አስመልክቶ አውደርዕይ ተካሂዷል። አውደርዕዩን የትምህርት ሚኒስቴር ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ያዘጋጀው ነው።

በአውደ ርዕዩ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተወጣጡ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ ከተለያዩ ስቲም ማዕከላት እና ከየክልሉ ትምህርት ቤቶች የተወጣጡ ተማሪዎች እና መምህራን የሰሯቸውን የፈጠራ ቴክኖሎጂዎች ይዘው ቀርበዋል።

94 ተማሪዎች ከስቲም ማዕከላት በኢንጂነሪንግ እና በሮቦቲክስ ዘርፍ የሰሯቸውን የፈጠራ ሥራዎች ያቀረቡ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ከሁሉም ክልሎች የተወጣጡ 50 ተማሪዎችና መምህራን የፈጠራ ሥራዎቻቸውን በማቅረብ ተሳታፊ ሆነዋል። በአውደርዕዩ የቀረቡት ሥራዎች በስምንት ዘርፎች ለውድድር የሚቀርቡ ሲሆን፣ ከስምንቱ ዘርፎች ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ የሚወጡ ተወዳዳሪዎች ሽልማቶች እንደሚበረከትላቸው መረጃዎች ያመላክታሉ።

አውደ ርዕዩ የኅብረተሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ በርካታ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የቀረቡበት ነው። እነዚህ አገር ተረካቢ ተማሪዎች እንዲሁም መምህራን የፈጠራ ሥራዎች የኅብረተሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ ከመሆናቸው ባሻገር እንደ አገር የተያዘውን ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚያግዙ ናቸው። በተለይ በቴክኖሎጂ ዘርፍ አገሪቱ ያላትን ተስፋ የሚያሳዩ መሆናቸው ተመላክቷል።

በአውደ ርዕዩ የፈጠራ ሥራቸውን ይዘው ከቀረቡት ስቲም ማዕከላት መካከል አንዱ የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ስቲም ማዕከል ነው። ከማዕከሉ የመጣው የአስረኛ ክፍል ተማሪው ዑመር አሊ የመኖ ማቀናበሪያ ማሽን ይዞ ቀርቧል።

ተማሪ ዑመር ቀደምሲልም የፈጠራ ሥራዎችን ይሰራ እንደነበር ይናገራል። በተለያዩ ጊዜያት የሰራቸውን የፈጠራ ሥራዎች በማሻሻል የተሻለ የፈጠራ ሥራ ይዞ እየወጣ መሆኑን ጠቅሶ፣ አሁንም ደግሞ የመኖ ማቀናበሪያ ማሽን መስራት መቻሉን ይገልጻል። ይህን ማሽን ለመስራት የተነሳሳበት ዋንኛ ምክንያት በሚኖርበት አካባቢ በቅርበት የተመለከተው የእንስሳት መኖ እጥረት ነው። በዚህ የተነሳ በእንስሳት እርባታ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ሲቸገሩ መመልከቱን ይገልጻል።

እሱ በሚኖርበት አካባቢ እንስሳት የሚያረቡ ሰዎች ለአንድ ጊዜ ፍጆታ የሚውል አንድ ኩንታል መኖ በ900 ብር ሲገዙ አስተውሏል። ዋጋው ከፍተኛ ስለመሆኑ በመግለጽ እጅጉ ሲቸገሩ ይመለከታል። ለእዚህ ችግር መፍትሔ ለማምጣት በማሰብ የመኖ ማቀናበሪያ ማሽን መስራት መቻሉን ገልጿል።

በአገሪቱ የእንስሳት እርባታ የተመጣጣነ የእንስሳት መኖ አቅርቦት አለመኖሩ እንስሳትን ለማርባትና የተፈለገውን ውጤት ለማምጣት እንዳላስቻለ የሚያመላክቱ ጥናቶች እንዳሉም ጠቅሶ፣ ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ችግር ፈቺ መፍትሔዎችን ማመንጨት እንደሚያስፈልግ ያመላክታል። እሱም መፍትሔ ያለውን ሀሳብ አፍልቆ የእንስሳት መኖ በቀላሉ ለማዘጋጀት የሚያስችል የፈጠራ ሥራ መስራቱን ይገልጻል።

የእንስሳት መኖ ማቀናበሪያ ማሽኑን ለእንስሳት መኖ አገልግሎት የሚውሉ መኖዎች ለማዘጋጀት እንደሚጠቅም ገልጾ፣ ረጃጅም ሳሮችንና የተለያዩ የሰብል አይነት አገዳዎችን በመጠቀም የእንስሳት መኖ ማዘጋጀት እንደሚያስችል ተናግሯል።

ተማሪ ዑመር እንደሚለው፤ ማሽኑ በአካባቢው ከሚገኙ እንደ ብረትና ብረት ነክ ነገሮች፣ ላሜራና ፌሮ የመሳሰሉት የተሰራ ሲሆን፣ ለመስራት ሁለት ወራት ገደማ ፈጅቷል። በኤሌክትሪክ፣ በሶላር እና በነዳጅ በሁሉም አማራጮች ሰዎች በሚፈልጉት መልኩ ሊሰራ ይችላል። በአንድ ሰዓት ውስጥ አምስት ኩንታል መኖ ፈጭቶ ያዘጋጃል።

ዲዛይናቸው ይለይ እንጂ እንደዚህ አይነት በሀገር ውስጥ የተሰሩ የመኖ ማቀነባበሪያ ማሽኖች እንዳሉም ጠቅሶ፣ የሚሰጡት አገልግሎት እሱ ከሰራው ማሽን ያነሰ፣ ዋጋቸው ግን የኅብረተሰቡን አቅም ያላገናዘበ መሆኑን ያብራራል። በገበያ ላይ እስከ 125ሺ ብር ድረስ እየተሸጡ መሆናቸውንም ይገልጻል።



በአውደርዕዩ የቀረቡ የፈጠራ ሥራዎች ሲጎበኙ

የእሱ ማሽን ግን ከእነዚህ ማሽኖች ከፍ ባለ መልኩ በጥራት የተሻለ ተደርጎ መሰራቱን ጠቅሶ፣ ከፍተኛ ወጪ የተደረገበት መሆኑንም አመልክቷል። ድጋፍ የሚያደርጉለት አካላት ካገኘ በቀላሉ በሚፈልገው መጠንና ልክ ሰርቶ በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ ለማቅረብም እንደሚችል አመላክቷል።

ይህን ፈጠራውን ሲሰራ የመምህሮቹና የወላጆቹ ድጋፍና እገዛ እንዳደረጉለት የሚናገረው ተማሪ ዑመር፤ እንደሱ የፈጠራ ሀሳብ ያላቸው ተማሪዎች ጊዜያቸውን በአግባቡ ተጠቅመው ከትምህርታቸው ጎን ለጎን ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራዎችን እንዲሰሩም መክሯል።

ሌለኛዋ በአውደ ርዕዩ የፈጠራ ሥራዋን ይዛ የቀረበችው ከኦሮሚያ ክልል ባሌ ዞን ሲናና ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጣችው መምህርት ሰሚራ አብዱልማሊክ ናት። መምህርት ሰሚራ፤ የሽንኩርት መፍጫ ማሽን ሰርታለች። ማሽኑን በሀገር ውስጥ መስራት መቻሉ ኅብረተሰቡ በቀላሉ ገዝቶ እንዲጠቀምበት ይረዳዋል ትላለች።

በአገራችን አብዛኛውን ጊዜ የምንጠቀመው የሽንኩርት መፍጫ ማሽን ከውጭ ሀገር የሚመጣና ዋጋውም በዚያ ልክ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሳ፣ እንዲህ አይነቱን ማሽን በማንኛውም ሰው ቤት በቀላሉ ማግኘት እንደሚከብድ መምህርቷ ተናግራለች። ይህን ማሽን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ቢቻል ሁሉም ሰው ገዝቶ ሊጠቀምበት ይችላል ብላ እንደምታስብ ትገልጻለች።

‹‹ሽንኩርት ያለ ማሽን በእጅ መክተፍ የሚያጋጥመውን ችግር በእጅጉ አውቃለሁ። ይህንን ችግር ለመፍታት የተሻለ ነው ያልኩትን አማራጭ ስፈልግ ያገኘሁት መፍትሔ በሀገር ውስጥ ማሽን መተካት ቢቻል የሚል ሆኖ ይህንን መፍትሔ ማፍለቅ ቻልኩ›› ስትል ታብራራለች። ‹‹መምህርት በመሆኔ የፈጠራ ሥራዎች በመስራት ለተማሪዎች አርአያ ለመሆን በማሰብ ይህንን የፈጠራ ሥራ መስራት ችያለሁ›› ትላለች።

የመምህርት ሰሚራ የሽንኩርት መፍጫ ማሽን ፈጠራ ስራዎች ሁለት አይነት ናቸው። አንደኛው በኤሌክትሪክ የሚሰራ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በባትሪ ድንጋይ የሚሰራ ነው። በተለይ በባትሪ ድንጋይ የሚሰራው የሽንኩርት መፍጫ ማሽን ኤሌክትሪክ በሌለባቸው ቦታዎች እና ኤሌክትሪክ በሚጠፋበት ጊዜ ጥቅም ላይ በማዋል ፈጣን መፍትሄ የሚያስገኝ መሆኑን አመልክታለች።

‹‹ብዙ ጊዜ ሽንኩርት ቤት ውስጥ ስንፈጭም ሆነ ገንዘብ ከፍለን ውጪ ስናስፈጭ አጋጣሚ ሆኖ መብራት ከጠፋ መብራት እስኪመጣ መጠበቅ አሊያም በእጅ ወደ መክተፍ የምንገባባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው›› ስትል ጠቅሳ፣ ይህ ማሽን ተክተን ብንጠቀም ጊዜአችንን በአግባቡ መጠቀም ያስችለናል›› ትላለች።

እነዚህ የሽንኩርት መፍጫ ማሽኖች በአካባቢዋ ከሚገኙ የወዳደቁ ቁሳቁሶች መስራቷን ትገልጻለች። የፕላስቲክ ሳህኖች፣ ዲናሞ፣ ቻርጀር፣ ትልቅ የባትሪ ድንጋይ እና ትናንሽ ቢላዎች ተጠቅማ መስራቷን ትገልጻለች። ‹‹ሁለቱንም ማሽኖች ተፈትሸዋል። እኔም ተጠቅሜባቸዋለሁ አይቼቸዋለሁ፤ በፍጥነትም ሆነ በምን መልኩ ከውጭ ከሚገባ የተሻሉ እና በየትኛውም አካባቢ ያለ ሰው ሊጠቀምበት ይችላል ›› ስትል ትገልጻለች።

መምህርቷ እንደምትለው፤ ሽንኩርት መፍጫ ማሽኑ በአንድ ጊዜ አንድ ኪሎ ሽንኩርት መፍጨት ይችላል። ከዚህ በላይ እንዲፈጭ አድርጎ መስራትም ይቻላል። ከውጭ ከሚመጣው በኤሌክትሪክ ከሚሰራውም ሆነ በእጅ ከሚሰራው ማሽን ጋር የተወሰነ ልዩነት አለው።

በሀገር ውስጥ የተሰራ ማሽን ልዩ የሚያደርገው በባትሪ ድንጋይ መስራት መቻሉ አንዱ ሲሆን፤ ዋጋውም የኅብረተሰቡን የመግዛት አቅም ያገናዘበና ተመጣጣኝ ነው። ኅብረተሰቡ የሽንኩርት ማሽኑን በቀላሉ ገዝቶ ሊጠቀምበት ይችላል፤ ሁሉም ሰው ሊኖረው የሚችል አይነት ነው።

ከውጭ የሚገባው በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰራው ሽንኩርት መፍጪያ ማሽን ዋጋ በአሁኑ ወቅት ከ3500 ብር በላይ እንደሚገመት ጠቅሳ፣ የእሷ የፈጠራ ውጤት የሆነው ማሽን ግን 500 ብር ዋጋ የተተመነለት መሆኑን አመላክታለች።

እነዚህን የሽንኩርት መፍጫ ማሽኖች አሁን ባሉበት ሁኔታ ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ይቻላል የምትለው መምህርቷ፤ ማሽኖቹ ሽንኩርቱን የሚፈጩበት ቢላዋ የተበየደ ነው፤ እነዚህ ቢላዎች ሽንኩርቱን ከፈጩ በኋላ እንዳይዝጉ በፕላስቲክ እንዲሆን የሚያደርጉ ሥራዎች ያስፈልጉታል። መሻሻል ያለባቸውን እያሻሻሉ ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግራለች።

ተማሪዎች የፈጠራ ሥራዎችን እንዲሰሩ ስታበረታታ መቆየቷን የምትናገረው ሰሚራ፤ እሷም የፈጠራ ሥራዎቿን እያሳደገች መምጣቷን ትገልጻለች። በተለይ መምህራን በአካባቢያቸው ላይ የሚያጋጥማቸው ችግር ነው ብለው በቸልታ ከሚያልፉ ለችግሩ መፍትሔ ያሉትን በማሰብ ማፍለቅ እንዳለባቸው ትገልጻለች። ‹‹ በቀላሉ ለችግሮቻችን በራሳችን መንገድ መፍትሔ መስጠት መልመድ አለበን። ለራሳችን ችግር የመፍትሔ አካል መሆን ያለብን እኛው ነን›› ስትልም አስገንዝባለች።

ከአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ስቲም ማዕከል የመጣው የ11ኛ ክፍል ተማሪው ይበልጣል ኮራ ሌላኛው የአውደርዕዩ ተሳታፊ ነው። ተማሪ ይበልጣል አውቶማቲካል የመስኖ ሲስተም መስራት ችሏል። ተማሪ ይበልጣል እንደሚለው፤ ሲስተሙ ያለሰው እርዳታ በራሱ ይሰራል። ማሳው በሚደርቅበትና ውሃ በሚያስፈልገው ወቅት ራሱ ሴንስ እያደረገ ውሃ እንዲያገኝ ያደርጋል፤ ማሳው በቂ ውሃ ሲያገኝ ደግሞ ውሃ እንደበቃውና እንደማያስፈልገው አውቆ በመዝጋት በራሱ የሚቆጣጠር ሲስተም የተገጠመለት ነው።

ይህ የመስኖ ሲስተም ሰውን ተክቶ የመስኖ ሥራ ይሰራል። ከዚህ ተጨማሪም ወፎችም ሆኑ ሌሎች እንስሳት ዘሩን ወይም ሰብሉን እንዳይበሉ ያደርጋል። በተገጠመለት ሴንሰር አማካኝነት ደውል በመደወል ከአካባቢው እንዲሄዱ ያባርራል። ሲስተሙ በማሳ ላይ የሚዘረጋ እንደመሆኑ በአካባቢ ላይ ውሃ እንዲኖር ከተደረገ በኋላ ያንን ውሃ ማሳው በሚፈልግበት ጊዜ ያጠጣል፤ የመስኖ ሥራውን ለማቀላጠፍ ያስችላል።

ሲስተሙ በኤሌክትሪክ ኃይልና በሶላር ኢነርጂ የሚሰራ ሲሆን ኤሌክትሪክ በሚጠፋበት ወቅት አውቶማቲክ እንደመሆኑ ወደ ሶላር ኢነርጂ ቀይሮ ይጠቀማል። በሶላር ኢነርጂ ብቻ መጠቀም ሲፈለግ ደግሞ ኤሌክትሪኩን በመተው ለመጠቀም እንዲቻል ሆኖ የተሰራ ነው።

ይህን የፈጠራ ቴክኖሎጂም በአካባቢው ላይ ከሚያገኛቸው የወዳደቁ ቁሳቁስ እንደሰራው ነው ተማሪ ይበልጣል የሚናገረው። ይህ ሲስተም በግብርና ዘርፍ በተለይ አርሶ አደሩን ከብዙ ድካምና ልፋት የሚታደግና የጎላ ፋይዳ ያለው ነው ይላል።

አርሶ አደሩ የመስኖ ማሳውን ውሃ ሲያጠጣ ለማሳው የሚያስፈልገውን ያህል ውሃ ሳይመጠን ቀርቶ ውሃ ማሳው ላይ እየበዛ ሲቸገር ማየቱ እንዲሁም አብዛኛውን የመስኖ ውሃ ለመሳብ ጥቅም ላይ የሚውለው ጀነሬተር መሆኑንም መመልከቱ ይህን የፈጠራ ሥራ ሰርቶ የአርሶ አደሩን ችግር ለመፍታት እንዳነሳሳው ይገልጻል።

ወደፊትም በፈጠራ ሥራው ላይ ማሻሻያ ማድረግ ባስፈለገ ጊዜ በማድረግ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እንዲሆን እንደሚሰራ የሚናገረው ተማሪ ይበልጣል፤ አርባ ምንጭ የስቲም ማዕከል ያገኘው ስልጠናና ድጋፍ ይህንን የፈጠራ ሥራ እውን እንዲሆን እንዳስቻለው አስታውቋል።

የፈጠራ ሀሳብ ያላቸው ተማሪዎች በውስጣቸው ያለውን ሀሳብ እንዲያወጡ የሚያነሳሳቸውና የሚያበረታቸው ድጋፍ የሚያደርግላቸው አካል ሊኖር እንደሚገባ ጠቅሶ፤ እንደዚህ አይነት የፈጠራ ሥራዎች የሚያቀርቡበትና የሚወዳደሩበት እድሎች መመቻቸታቸው ጥሩ እድል እንደሚፈጥር ተናግሯል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የቀይ ባሕር ቀጣና እና የኢትዮጵያ ሚና

**አስቴር ኤልያስ**

የስህበት ማዕከል የሆነው የቀይ ባሕር ቀጣና ቀድሞም ቢሆን የየአገራቱን ትኩረት ሲስብ የነበረና አሁንም ድረስ እየሳበ ያለ አካባቢ ነው። አቅም በፈቀደ መጠን ቀጣናውን ለመቆጣጠር የማይተኙ አገራት በርካታ ናቸው። ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ባለቤት የሆነችውና የቀይ ባሕር ባለይዞታ መሆኗ የሚነገርላት ኢትዮጵያም ወደዚህ ቀጣና ለመቀላቀል የባሕር በር ሊያስገኝላት የሚያስችላትን የስምምነት ፊርማ ከራስ ገዟ ሱማሌላንድ ጋር በማኖር አንድ ብላ መጀመሯ የሚታወቅ ነው።

የባሕር በር ለማግኘት የሚደረገው እንቅስቃሴ ብዙዎች እንደሚያስቡት ሸቀጥ ማጓጓዣ ብቻ አይደለም፤ ሕልውና ማስጠበቂያም ጭምር እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ይስማሙበታል። ከሌሎች አገራት ጋርም ሊያስተካክል የሚችል እንደሆነም የሚነገር ነው። ይህ ኢትዮጵያ ልታገኘው ፊርማዋን ያኖረችለት በቀይ ባሕር ቀጣና ያለው አካባቢ እንዴት ይገለጻል? የቀጣናው የትኩረት ማዕከልነቱ እንዴት ይታያል? ስንል ምሁራንን ጠይቀናል።

ካነጋገርናቸው ምሁራን አንዱ የታሪክ ምሁሩ አቶ ዳኛው ገብሩ ናቸው፤ እርሳቸው ኢትዮጵያ በዓባይ ጉዳይም ሆነ በቀይ ባሕርም ተሳትፎ የነበራትና ያላት አገር ናት ሲሉ የዓባይ ወንዝን ጨምረው ይጠቅሳሉ። የሁለቱም የትኩረት አቅጣጫዎች በዋናነት የሚያርፈው ኢትዮጵያ ውስጥ ነውም ይላሉ። የቀይ ባሕርም ሆነ የዓባይ ጉዳይ የችግር መነሻውን የሚያደርገው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ሲሉ ጠቅሰው፤ ለዚህ ምክንያታቸው ደግሞ ኢትዮጵያ የቀይ ባሕርም የዓባይም ባለይዞታና ባለቤት በመሆኑዋ ነው ይላሉ።

እሱ ብቻ ሳይሆን ከሌሎቹ አገሮች ጋር ኢትዮጵያ ስትነጻጸር ተጽዕኖ ልትፈጥር ትችላለች ተብሎ በሌላው የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ግምት የተሰጣት ናት ሲሉም ያክላሉ። ምናልባትም ኢትዮጵያ የምስራቅ አፍሪካ አጠቃላይ ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ የመፍጠር አቅም ያላት አገር ናት፤ ከዚህ የተነሳ ዓለም በትኩረት የሚመለከቷትና አልፎ አልፎ አንዳንዶቹም በስጋት የሚያይዋት እንደሆነችም ያመለክታሉ።

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መምህሩ ጥላሁን ኤርዱኖ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በቀይ ባሕር ላይ ምንም አይነት ሚና የላትም። የነበራትን ሚና ካጣች ቆይታለች ይላሉ። አንደኛ በአሰብ አካባቢ በርካታ ሀብት ነበረን። አሰብ ላይ ያለን ወደብ ብቻ አልነበረም፤ የነዳጅ ማጣሪም ጭምር ነበር። ከዚህ ሌላ በጣም ጠንካራ የነበረ የባሕር ኃይልም ነበረን ሲሉ ቁጭታቸውን ይናገራሉ።

በእርግጥ ቀደም ሲል ይላሉ ጥላሁን (ዶ/ር)፣ በቀይ ባሕር አካባቢ ኢትዮጵያ የነበራት ተጽዕኖ ከፍተኛ ነበር። ያንን ተጽዕኖ ይዛ ቆይታ ቢሆን ዛሬ ላይ የት በደረሰች ነበር? የገነባነው ጠንካራ የባሕር ኃይል ነበርና በሱማሊያ አካባቢ የሚታየው የባሕር ላይ ውንብድና ባልኖረም ነበር። ይሁንና አሁንም ቢሆን ተስፋ የሚቆረጥበት አይደለም። በቀጣይ ተጽዕኖ ይኖረናል የሚል እምነት አለኝ። እኔ ተስፋ አልቆርጥም። ይህ ግን የሚወሰነው የኢትዮጵያ መንግስት ሕዝቡን የሚይዝበት አያያዝና ሕዝቡ ለሰላም ቁርጠኛ መሆን ሲችል ነው።

አቶ ዳኛው ገብሩ አክለውም ውሃ የዓለም ፖለቲካ ቁጥር አንድ አጀንዳ ነው የሚሉት የታሪክ ምሁሩ፣ ውሃ ከነዳጅም ከወርቅም የሚበልጥ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ሰማያዊ ወርቅ ነው ተብሎ እንደሚነገር ይገልጻሉ። እንደ እርሳቸው አባባል፤ ሌሎቹ ሀብቶች በሌላ ሊተኩ ይችላሉ። ውሃ ግን የማይተካ ሀብት ነው። ምናልባትም በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሶስተኛው የዓለም ጦርነት የሚነሳ ከሆነ መነሻው ውሃ ነው ብለው ብዙዎቹ ምሁራን በስጋትነት እንደሚተነብዩ ይናጋራሉ። ምክንያቱ ደግሞ የዓለም ሕዝብ በውሃ ጥማት ውስጥ መኖሩ ነው።

እንደሚታወቀው ከዓለም ክፍል 71 በመቶ የሚሆነው ውሃ ነው። ከዚህ ውስጥ በቀጥታ ጥቅም ላይ መዋል የሚችለው የውሃ መጠን ሶስት ነጥብ አምስት በመቶው ብቻ ነው። 96 ነጥብ አምስት በመቶ የሚሆነው ውሃ በቀጥታ ለአገልግሎት የማይውል ውሃ ነው። ውሃው እንኳ ቢኖር ለጥቅም ማዋል የሚቻለው በከፍተኛ ወጪ ነው።

ታዲያ ይላሉ አቶ ዳኛው፣ ዓለም የሚሻኮተው ሶስት ነጥብ አምስት በመቶው ውሃ ላይ ነው። ከሶስት ነጥብ አምስት በመቶ ከሚሆነው ውሃ ውስጥ ደግሞ 61 በመቶ የሚሆነው ውሃ የሚገኘው ሰው በማይኖርበት በአርክቲክና በአንታርክቲክ አካባቢ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ዓለም የሚራኮተው ከአንድ ነጥብ አምስት በመቶ ያልበለጠ ድርሻ ባላቸው በኢትዮጵ ውስጥ እንደሚገኙ አይነት አገር አቋራጭ ወንዞች ላይ እንደሆነ ይናገራሉ።

እንደ ታሪክ ምሁሩ ገለጻ፤ ዓለም፣ በውሃ አስተዳደር፣ አጠቃቀምና አያያዝ ላይ ከፍተኛ የሆነ ቀውስ ውስጥ ነው። በዚህ ምክንያት ደግሞ አገሮች ይጣላሉ፤ በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ አገሮች የሚዋጉት በውሃ ምክንያት ነው። ብዙ አገሮች የሰላም እጦታቸው እና የችግር መነሻቸው ውሃ ነው። ምናልባትም ወደፊት የውሃ እጥረቱ በርካታውን የዓለም ሕዝብ ወደ እልቂት ውስጥ ያስገባዋል ተብሎ ይጠበቃል።

ስለዚህ የውሃ ፖለቲካ በዓለም ላይ ትልቅ አጀንዳ ነው ሲሉ ጠቁመው፤ ኢትዮጵያም ያለችው በዚሁ የውሃ ፖለቲካ ውስጥ ነው ይላሉ። ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያን ስንመለከት በሁለቱም ጉዳዮች ላይ ማዕከል የሆነች አገር ናት። የመጀመሪያ የኢትዮጵያን የውጭና የአገር ውስጥ ፖለቲካ ሲወስን የቆየው የዓባይ እና የቀይ ባሕር ጉዳይ ነው።

ኢትዮጵያ ባሳለፈችባቸው በውጭ ፖሊሲ፣ የውጭ ግንኙነት፣ የውስጥ ችግሯና ግጭቷ አባባሽና መነሻው የዓባይና የቀይ ባሕር ጉዳይ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ እነዚህን ሀብቶቿን በብዛት ሳትጠቀም የዘለቀች፤ በተለይም ዓባይን ሳትጠቀምበት የቆየችበት ውሃ ሲሆን፣ እስካሁንም ድረስ ጠላት ሲጠራብን እዚህ ደርሷል። በእርግጥ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ለመጠቀም አቅም አልነበረንም የሚሉት አቶ ዳኛው፣ ሲደረግ የነበረውም ሙከራ ጥቂት ነበር ብለዋል።

የታሪክ ምሁሩ አቶ ዳኛው፣ ሌላኛው ጉዳይ ቀይ ባሕር ነው ይላሉ። ቀይ ባሕር ጥንትም ቢሆን የተወሰነው ክፍል የኢትዮጵያ ይዞታ እንደነበር ይታወቃል። ምንም እንኳ ሰዎች የወደብን ጉዳይ ከሸቀጥ ጋር ቢያመሳስሉትም ቀይ ባሕርን ያጣነው አለአግባብ ነው፤ እኛን ጨምሮ ዓለም በቀይ ባሕር ላይ ያለው ፍላጎት የወደብ ብቻ አይደለም፤ የሕልውናም ጉዳይ ጭምር ነው ይላሉ።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የባሕር በር ትፈልጋለች ሲባል የወደብ ጉዳይ ብቻ ሆኖ አይደለም። እንደ አገር ሕልውናዋን ጭምር ለማስጠበቅ በማሰብ ነው። ስለዚህ የቀይ ባሕር ጉዳይ የወደብ ጉዳይ ብቻ እንዳልሆነ መረዳቱ የግድ ነው። ቀይ ባሕር የዓለምን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቀውስ ሊፈጥር ወይም ደግሞ ሰላማዊ ሊያደርግ የሚችል ወሳኝ የሆነ ቀጣና ነው።

ኢትዮጵያ ይህን ባሕር በስህተት አጥታው ቆይታለች። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ቀይ ባሕርን እንደሌሎቹ ቀጣናውን ፈላጊ አገራት መጋፈጥ ያስፈልጋል። ይህን የምናደርገው ደግሞ ለአገራችን ሰላም ሲባል ነው። ቀይ ባሕርን ስናስተውል በርካታ ጸጋዎች ያሉት ነው። በተለይም ሸቀጦችን እና ጥሬ ሀብቶችን ከአንዱ ቦታ ወደሌላው ቦታ ለማጓጓዝ ርካሽ የሚባለው የውሃ ላይ ትራንስፖርት ነው። የዓለም ሸቀጥና ጥሬ ሀብት በውሃ ላይ መጓጓዝ ካለበት ደግሞ ዋናው ማዕከሉ ቀይ ባሕር ነው። ከዚህም በተጨማሪ ቀጣናው ስትራቴጂካዊ ቦታ ነው።

ከፍተኛ ቁጥር ያለው የዓለም ሕዝብ የሚኖርበት ይህ ቀጣና፣ ከፍተኛ የሸቀጥ ዝውውር የሚካሔድበትና በተለይም የአፍሪካ ሰፊ ጥሬ ሀብት የሚገኝበትም ነው የሚሉት አቶ ዳኛው፣ ሰፊ ገበያም ያለው መሆኑን ያስረዳሉ። በንግዱ ስራ አትራፊ መሆን የሚቻለውም ዓለም በዚህ በቀይ ባሕር ላይ ሲጓጓዝ ነው ይላሉ። ይሁን እንጂ ቀይ ባሕር አሁን ያለው በችግር ውስጥ ሲሉ ይናገራሉ።

ዶክተር ጥላሁን እንደሚሉት በዙሪያችን ያለው ወደብ በሙሉ ማለት ይቻላል በአረብ ሊግ አባል አገራት የተያዘ ነው። ኤርትራም ተለዋጭ የአረብ ሊግ አባል መሆኗ ሊረሳ አይገባም። ስለዚህ የራሳችን ወደብ የሚያስፈልገን መሆኑ የግድ ነው ይላሉ። የምንጠቀምበት የጅቡቲ ወደብ እንደመሆኑ የቀይ ባሕር ቀጣና ካለበት ከፍተኛ ትኩረት የተነሳ በጊዜ ሒደት ጅቡቲ ተጽዕኖ ውስጥ ልትገባ ትችላለች።

ሱማሊያም ብትሆን የፈረሰች አገር ከመሆኗ

> **የዓለም ሸቀጥና ጥሬ ሀብት በውሃ ላይ መጓጓዝ ካለበት ደግሞ ዋናው ማዕከሉ ቀይ ባሕር ነው። ከዚህም በተጨማሪ ቀጣናው ስትራቴጂካዊ ቦታ ነው**

በተጨማሪ አልሸባብም እያስቸገረ ነው። ሌላውም ወደብ የራሱ ተጽዕኖ ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪ የቀድሞ ቅኝ ገዥዎች የእጅ አዙር ተጽዕኖ ያለበት ነው ሲሉ ያስረዳሉ። ስለዚህ እኛ ወደብ እንድናገኝ ማድረግ ያለብንን ሁሉ በእቅድ በመያዝ ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀስ አለብን። በአሁኑ ወቅት ግን እኛ በቀይ ባሕር ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ መፍጠር አንችልም ብለዋል።

የታሪክ ምሁሩ አቶ ዳኛው እንደሚገልጹት ከሆነ ደግሞ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለቀይ ባሕር የተሰጠው ትኩረት በሶስት መንገድ የሚፈረጅ ነው ይላሉ። የመጀመሪያዎቹ በቀይ ባሕር ጉዳይ ሃያ አራት ሰዓት የማያንቀላፉ አገራት ናቸው፤ ሁለተኞቹ ደግሞ ሃያ አራት ሰዓት የሚያንቀላፉ ሲሆኑ፣ ሶስተኞቹ ደግሞ በቀይ ባሕር ዙሪያ ችግር ጠንሳሾች ናቸው። ይህንን ሲያብራሩ እንደሚሉት፤ አንደኛ ሃያ አራት ሰዓት ከቀጣናው አይናቸውን ለአፍታ የማያነሱ አገራት ሲስተዋሉ ሁሉም በሚያስብል ደረጃ ተረባርበው በቀይ ባሕር አካባቢ ከጅቡቲ እስከ ሱማሊያ ድረስ ወደብና የጦር ሰፈር እየተከራዩ ተቀምጠዋል።

ይህ ሲጤን ወደብ ፍለጋ አይደለም። ለፖለቲካዊ፣ ለኢኮኖሚያዊና ለወታደራዊ አቅም ስትራቴጂክ ቦታ የመፈለግና የመያዝ ጉዳይ ጭምር ነው። ምክንያቱ ደግሞ ቀይ ባሕር ላይ በመራኮት ላይ ያሉ አገሮች ወደብ ሞልቶ የተረፋቸው ናቸው። እነዚህ የማያንቀላፉ አገሮች የአፍሪካንና የኢስያን ኢኮኖሚ ሊቀራመቱ፣ ሰፊ የሆነውን የሰው ጉልበት ሊበዘብዙና ገበያውን ሊጠቀሙ የሚችሉ አገሮች ሲሆኑ ለአፍታ እንኳ የማያሸልቡ ናቸው።

የታሪክ ምሁሩ በሁለተኛ ደረጃ የፈረጇት ደግሞ ሃያ አራት ሰዓት የሚተኙቱን ሲሆን፣ እነርሱም የአካባቢው አገሮች ናቸው ብለዋል። ለአብነትም ሲጠቅሱ ሱዳን፣ ሱማሊያ፣ የመንም ጭምር እንደሆኑ ገልጸው እነርሱም እንቅልፋሞች ናቸው ሲሉ ይገልጿዋቸዋል። እነዚህ የአካባቢው አገራት እንቅልፋሞች ባይሆኑ ኖሮ፤ በተናጠል ጥቅማቸውን ማስከበር ባይችሉም፤ ሕብረት በመፍጠር ጥቅማቸውን ያስከብሩ እንደነበር አስረድተዋል።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ እየጠየቀች ያለችው ኅብረት እንፍጠር ነው። ሰጥቶ በመቀበል መርህ አንድነታችንን በማጠናከር ጥቅማችንን እናስከብር ነው። ኢትዮጵያ ይህንን ስትል የተለያዩ አገሮች የሚያይዋት በስጋት ነው። የአካባቢው አገራት ቀድሞም ቢሆን ደካማ ናቸው። በተናጠል መራመዳቸው ደግሞ የሌሎቹ ሃያ አራት ሰዓት የማይተኙ አገሮች መረማመጃ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይህ ደግሞ እየሆነ ያለና ወደፊትም አይቀሬ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ዳኛው አገላለጽ፤ በሶስተኛው ላይ የሚፈረጁት ደግሞ በቀጣናው ችግር የሚጠምቁ አካላት ናቸው። በአካባቢው ድሮን ጭምር በመጠቀም ዓለምን የሚያስቸግሩ፤ ቀጣናውንም የሚያምሱ አካላት አሉ። ከዚህ የተነሳ ቀይ ባሕር ወንበዴዎች የሚፈነጩበት ቀጣና ነው። ከዚህ የተነሳ አካባቢው የተጨናነቀ ነው።

የመን የፈረሰች አገር ናት፤ በተመሳሳይ ሶማሊያም እንደዚያው ናት። ሱዳንም በትርምስ ውስጥ የምትገኝ ያልተረጋጋች አገር ናት። ከዚህ በተጨማሪ ቀይ ባሕርን ስናነሳ የአረብና የእስራኤል ግጭት ያለበት አካባቢ ነው። ሁለቱ ደግሞ የበረታ አለመግባባት የሚስተዋልባቸው ናቸው።

አቶ ዳኛው፣ በዚህ በችግር ውስጥ ባለ ቀጣና የሚገኙ ሀገራት የሕልውና ስጋት አለባቸው ይላሉ። ስለዚህ እኛም ሸቀጦቻችንና ጥሬ ሀብቶቻችን በሰላም በባሕሩ ላይ እንዲተላለፉ ባለቤት በመሆን ጥቅማችን ማስከበር መቻል እንዳለብን ይገልጻሉ። ሁለተኛው ደግሞ የትኛውም አገር እኛን እንዳይተነኩሰን የራሳችንን ኃይል ቀይ ባሕር ላይ መፍጠር መቻል ይጠበቅብናል ሲሉ ያመለክታሉ።

ለዚህ ምክንያታቸው ደግሞ ቀይ ባሕር ከወደብ በዘለለ የኢትዮጵያ የሕልውና ጉዳይ መሆኑ ነው፤ በመሆኑም ቀይ ባሕር ላይ መውጫ ኮሪደር ያስፈልገናል በሚል የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የወሰዱት ወሳኝ አቋም የእኔም ነው ይላሉ። ይህ ደግሞ ትክክለኛ ነገር ነው።

እኛ የቀይ ባሕር ባለቤቶች ነን፤ ስለሆነም የተወሰደብንም ቀይ ባሕር ይዞታ መመለስ አለበት፤ ጥያቄ ስናነሳ መላ ኢትዮጵያዊ ሊተባበረን ይገባል፤ ምክንያቱም ቀይ ባሕር ላይ ድርሻ የማይኖረን ከሆነ ዘለቄታ ያለው ሕልውና ሊኖር አይችልም ብለዋል።

# ከሀገር ውጪ ካለ ወዳጅ ዘመድ ስጦታዎችን በቀላሉ ወደ እጅ

**ሰሚራ በርሀ**

ዓለም በርካታ ቴክኖሎጂዎችን አስተዋውቃናለች። ሰዎች የሚገለገሉባቸው፣ ሕይወታቸውን የሚያቀሉባቸው ፣ አጃኢብ የሚያሰኟቸው ቴክኖሎጂዎች በቅርበት ማየት ችለናል። ከእነዚህም መካከል አንዱ የሆነውን የእጅ ተንቀሳቃሽ ስልክ እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል። ሰዎች ቀደም ባሉት ዘመናት አጠገባቸው የሌለን አርቆ የሚገኝ ወዳጅ ዘመዳቸውን የሚያገኙትና ናፍቆታቸውን የሚወጡት አንድም በስልክ ድምፃቸውን በመስማት ካልሆነም ደብዳቤ በመጻፍ እና በፖስታ ቤት እንዲደርስ በማድረግ ነበር። ይሄም ምን ያህል ጊዜን እንደሚወስድና ሰፊውን የሰዎችን ሀሳብ በቁንጽል መልዕክት ብቻ የሚተላለፍበት እንደነበር አንዘነጋውም።" በስልክ አነጋግሪኝ በቀጭኑ ሽቦ ትዝታ እንዲመጣ ደርቦ ደራርቦ..." ተብሎም ተዜሞለታል የቤት ስልክ።

አሁን ላይ ደግሞ ዘመኑ ባፈራቸው ዘመናዊ ተንቀሳቃሽ የእጅ ስልኮች በድምፅ ብቻ ሳይሆን በምስል ተደግፎ እየተያዩ ሀሳብን ከነስሜቱ መግለጽ የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ሀሳብን በተለያየ መንገድ በአጫጭር የጽሁፍና የድምጽ መልዕክት በቀላሉ ማስተላለፍ ተችሏል። በተለያየ የገበያ ስፍራ ላይ ሳይገኙ ግብይትን መፈጸም እንዲሁ ዛሬ ቀላል የሆነበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። እንኳንስ በሀገር ውስጥ ከውጪ ሀገር ጭምር ከወዳጅ ዘመድ የተላከ ስጦታ ሳይቀር አለንበት እቤታችን ድረስ የሚመጣበት ዓለም ወደ አንድ ኗስነት እየተቀየረች ያለችበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። ብዙ የሚታዩ ከጊዜው ጋር አብረው የዘመኑ ነገሮች ሕይወትን ቀለል እያደረጉ ይገኛሉ። ከሀገር ውጪ በገበያ ላይ በአይን ያዩትንና የተመኙትን የራስ ማድረግ ዛሬ ቀላል ነው። ዕድሜ ለኦላይን ገበያ።

የዓለም ሀገራት ኑሯቸውን ያደረጉ ሰዎች በተለያዩ ወቅቶችና በዓላት የትራንስፖርት አማራጮችን በመጠቀም ወዳጆቻቸው ወደሚገኙበት ቦታ በመሄድ ጊዜን ያሳልፋሉ ። ለወዳጅ ዘመዶቻቸውም ስጦታ የሚያበረክቱት አንድም በሚመጡበት ወቅት ያመጡትን በመስጠት ይሆናል። መምጣት ያልቻለ ሰው ደግሞ መልዕክቱ በትክክል ይደርስ ወይም አይደርስ ይሆን የሚል ጭንቀት ታክሎበትም ቢሆን ፖስታ ቤትን በአደራ መልዕክት አድራሽነት ይጠቀማሉ። ከዚህ ውጪ ሌሎች አማራጮች ብዙም አይታወቁም ነበር። ጊዜ ለሁሉም ነገር መፍትሄ አለውና አሁን ስጋትን የሚቀንስ የመረጡትን ስጦታ እቤት ድረስ የሚያደርስ አገልግሎት እደጃችን ደርሷል።

ራሔል ፍቅሬ በርቀት የሚገኙ ወዳጅ ዘመዶች ፣ ቤተሰቦች እርስ በእርስ እንዲደጋገፉ በማንኛውም ወቅት ስጦታ እንዲለዋወጡ የሚያደርግ መፍትሄ ይዛ ቀርባለች። ስያሜው « ቤተሰብ ጊፍትስ » ይሰኛል። የተለያዩ ሰዎች ፍላጎት ላይ ያተኮሩ ስጦታዎችን በቦታ ርቀት ምክንያት መስጠት ላልቻለ ሰው ልክ እንደባለቤት በመሆን የታዘዘውን ስጦታ ለተሰጪው ባለበት ያደርሳል ። ቤተሰብ ጊፍት የተቋቋመበት ዓላማ በርቀት የሚገኘውን ሰው ፍላጎት ለማሳካት፤ በተለያዩ ሁነቶች የታዘዟቸውን ስጦታዎች በሚፈለግበት ቀን ለታዘዘላቸው ሰዎች ማድረስ እና ለስጦታ ተቀባዩም ደስታን መፍጠር ነው።

እንዲህ ያለ የሥራ ሀሳብ እምብዛም በሀገራችን ያልተመደ በመሆኑ አጀማመሩ ምን ይመስል እንደነበር ራሔል እንዲህ ትገልጻለች። « አብዛኛዎቹ ደንበኞቻችን ከሀገር ውጭ የሚኖሩ ናቸው። የጀመርንበት ምክንያት በቅርብ የምናውቃቸው ከሀገር ውጪ የሚገኙ ሰዎች ለወዳጆቻቸው የዓመት በዓል ሲሆንና ለተለያየ ፕሮግራም ስጦታ መስጠት እየፈለጉ ነገር ግን መንገዱን ማግኘት ባለመቻላቸው ሲቸገሩ በማየታችን ነው » ትላለች። ራሔል በዚህ ዙሪያ ያለውን ክፍተት የሚሞላ በውጪው ዓለም ያለውን ተመክሮ በማየት ለሀገራችን አዲስ የሆነ ሀሳብ ይዛ ብቅ ብላለች።



ለወዳጅ ዘመድ ከውጪ ሀገር ካለ ቤተሰብ በኦንላይን ገበያ የሚበረከት ስጦታ፤

የቤተሰብ ጊፍት ሰዎች ናፍቆታቸውን የሚወጡበትን፣ በአካል ቢኖሩ ለወዳጆቻቸው ማድረግ የሚፈልጉትን በውጭ ያሉ ወላጆች ለልጆቻቸው ልደት ፣ ለባለቤታቸው የጋብቻ በዓል፣ ልጆች ደግሞ ለወላጆቻቸው የበዓል ስጦታ መስጠት ሲፈልጉ በዚህ የቤተሰብ ስጦታ አገልግሎት አማካኝነት የሚፈልጉትን የስጦታ አይነት ለሚፈልጉት ይልካሉ። ኧረ እንዳውም የመልካም ቀን ምኞታቸውን በስጦታ የታጀበ ማድረግ ከፈለጉ የቤተሰብ ጊፍትን እንደአማራጭ ይጠቀማሉ። ራሔል ለዚህ አገልግሎት ምቹ ሆኖ ያገኘችው ቤተሰብ ስጦታ የሚል ይፋዊ ድህረገጽ ነው። በሌሎች የማህበራዊ ገጾች እንዲሁ በመጠቀም ሰዎች የስጦታ ጥቅሎችን በማዘጋጀት እንዲሁም ደንበኞቻቸው የሚፈልጉትን ስጦታ በማካፈል ለሚፈለገው ሰው ባለበት ቦታ ያደርሳሉ።

የስጦታ ጥቅሎቹ የመልካም ቀን ምኞት፣ የበዓል ጥቅል በሀገራችን በስፋት በሚከበሩ የአዲስ አመት፣ ገና፣ የፋሲካ በዓል፣ ረመዳን ፤ ልደት፣ ሠርግ፣ የጋብቻ ዓመታዊ በዓል ያካትታል። በእነዚህ ሁነቶች ለስጦታ የሚቀርቡት አበባ፣ ልዩ ልዩ ጣፋጭ ምግቦች፣ የተለያዩ ስጦታዎች ናቸው። ለበዓላት ወቅት ደግሞ በግ፣ ዶሮ እና ሌሎች ለበዓል ፍጆታ የሚውሉ ግብዓቶችን በስጦታ መልክ ይቀርባሉ።

ከውጭ ሀገር የሚኖሩ ሰዎችን ትእዛዝ ተቀብሎ በሀገር ቤት ለሚገኙ ሰዎች ማድረስ መልካም ሀሳብ ቢሆንም ከሌሎች ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ ያለው የክፍያ መንገድ አስቸጋሪ እንደነበር ራሔል ታስታውሳለች ። " ይህንን ስራ በጀመርንበት ወቅት አስቸጋሪው የነበረው የክፍያ ስርዓት ነበር። እዛ ሀገር ያለ ሰው ወደዚህ ቀጥታ ክፍያ የሚከፍልበት መንገድ አልነበረም። በወቅቱ የነበረውም የክፍያ መንገድ ይቆያል። ክፍያ ካልተፈጸመልን ደግሞ አገልግሎቱን መስጠት ከባድ ነው። » በማለት የምትገልጸው ራሔል አሁን ግን እንደቴሌብር ባሉ የክፍያ አማራጮች እንዲሁም በሀገር ውስጥ ባንኮች ቀጥታ ወደኢትዮጵያ ክፍያ መፈጸም የሚቻልባቸው አማራጮች መፈጠራቸውን ትናገራለች። አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች መኖራቸው የራሔልን ስራ ቀላል አድርጎላታል።

ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች ላይ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም ቤተሰብ ጊፍትን በመጠቀም ስጦታቸውን ለወዳጆቻቸው ይልካሉ። « ደንበኞቻችን በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ናቸው። በዱባይ፣ በአሜሪካ በፈረንሳይ፣ በጀርመን እና ሌሎች ሀገራት ላይ የሚገኙ ደንበኞች አሉን። የውጭ ሀገር ዜጎች ሆነው በኢትዮጵያ በስራ ላይ ያሉ ሰዎች ወይም ቤተሰቦቻቸውም በእኛ በኩል ስጦታ ይልካሉ። » በማለት በተለያዩ የዓለም ሀገራት ያሉ ደንበኞችን ፍላጎት እያረካች መሆኑን ትናገራለች።

አንድ ሰው ለወዳጁ ስጦታ ለመስጠት ሲያስብ ስለሚገዛው እቃ አስቀድሞ ያስባል። ወዳጁ ያስደስተዋል ያለውን የስጦታ አይነት ከመረጠ በኋላ የእቃው ጥራት ላይ እርግጠኛ መሆን ይገባል። ምክንያቱም ስጦታ የሚሰጠው ለሚወዱት ሰው ነውና። « ለስጦታ የምንገዛቸውን እቃዎች የምንገዛባቸው ቋሚ አቅራቢዎች አሉን። በተቻለን መጠን በጣም ከሚታወቁ እና ስም ካላቸው አቅራቢዎች እንገዛለን። » በማለት የምታብራራው ራሔል በዚህ ወቅት ስጦታውን መስጠት የፈለጉ ደንበኞቻቸው ፍላጎት ምን እንደሆነ በቅድሚያ ይጠየቃሉ። ስጦታውን ካዘጋጁ በኋላ አዲስ አበባ ውስጥ ከሆነ ያለምንም ክፍያ ስጦታው ለሚገባው ሰው በሰዓቱ ያደርሳሉ። ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ ባሏቸው ኤጀንቶች አማካኝነት እንዲሁ በባህርዳር፣ ደብረዘይት፣ አዳማ፣ ሻሸመኔ እና ሀዋሳ ላይ አገልግሎቱን ያቀርባሉ ።

በተለያየ መንገድ አገልግሎት የመስጠት ስራ ዘርፉ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የደንበኞቻቸውን ፍላጎት በማሟላት ደንበኞቻቸው በሚሰጧቸው ምላሽ የስራቸውን ስኬታማነት ያረጋግጣሉ። የቤተሰብ ጊፍት ደግሞ ልክ እንደቤተሰብ በመሆኑ በሚሰጡት አገልግሎት ቤተሰብን ከቤተሰብ ያቀራርባሉ። « ስጦታ ሲሰጥም ሆነ ስንቀበለው በጣም ደስ የሚል ነው። ሌሎች ሰዎች ደግሞ የፈለጉትን በማሳካት ለሰዎች ደስታ መፍጠር በጣም የሚያስደስት ስራ ነው። » በማለት ራሔል ስራዋን ትገልጻለች።

ራሔል በዚህ ስራዋ የሰዎችን ፍላጎት ከማሟላት ባለፈ በርካታ የስራ እድልን መፍጠር ችላለች። « የምናቀርባቸውን ስጦታዎች የሚያቀርቡልን ደንበኞች አሉን። እነዛን ስጦታዎች ደግሞ አዘጋጅተን ለሚመለከተው ሰው ባለበት ቦታ የሚያደርሱልን ሰራተኞች አሉ። ስለዚህ ለብዙ ሰዎች የስራ እድል መፍጠር ችለናል ብዬ አስባለሁ። » ትላለች።

የቤተሰብ ጊፍት ከተመሰረተ ከሁለት ዓመት በላይ ያስቆጠረ ሲሆን ሰዎች ስጦታዎችን ለማዘዝ ይፋዊ ድህረ ገጽ እና ሌሎች አማራጭ የማህበራዊ ገጾችን በመጠቀም ይስተናገዳሉ። እንደቤተሰብ ጊፍት ለማሳካት የሚፈልጓቸው እቅዶች እንዲሁ አሉ። « አሁን ላይ እያስተናገድን ያለነው ከውጭ ሀገር ከሚገኙ ደንበኞቻችን ጋር ነው ። በሀገር ውስጥ ያሉ ደንበኞችን ማሳተፍ እንፈልጋለን ። ወደፊት የራሳችንን የስጦታ ስፍራ ገንብተን ሰዎች ራሳቸው መጥተው የሚፈልጓቸውን ስጦታዎች መርጠው በሚፈልጉት መንገድ አዘጋጅተው እንዲወስዱ የማድረግ ሀሳብ አለን። ለዚህም ስራ ሰፊ የሆነ ቦታ ያስፈልጋል። ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል አስፈላጊው ድጋፍ በዚህ በኩል ቢደርግልን የሚል ሀሳብ አለን። »

ራሔል ይህን ስራ የጀመረችው በአካባቢዋ ባስተዋለችው በሰዎች ፍላጎት እንደሆነ በማስታወስ የራሳቸውን ስራ መስራት ለሚፈልጉ ወጣቶችም ሆነ ሴቶች ተሞክሮዋን ታጋራለች። « ስራ ፈጣሪ መሆን የሚፈልጉ ሰዎች መጀመሪያ አካባቢያቸውን ማስተዋል፤ ሰዎች እንደችግር የሚያነሱትን ነገር ትኩረት ሰጥተው ማዳመጥ አለባቸው። ዋናው ነገር ስራውን መጀመር ቢሆንም በቀጣይ ደግሞ ስራው ስኬታማና ተመራጭ እንዲሆን ዋጋ መክፈል፣ በቂ ጊዜ መስጠት አለባቸው። » በማለት አብዛኛዎቹ ሰዎች የሥራ ሀሳብ ኖሯቸው ቢጀምሩትም ለሥራው የሚገባውን ጥረት ባለማድረጋቸው ብዙም ሳይቆዩ እንደሚያቋርጡት ትገልጻለች። « በሀገራችን በርካታ ወደሥራ መቀየር የሚችሉ ፤ መፍትሄ የሚፈልጉ ጉዳዮች ስላሉ መፍትሄውን ፈጥረው ለመስራት ፍቃደኛ ከሆኑ መለወጥ ይችላሉ ። " ዋናው ውስጣዊ የሥራ ተነሳሽነት መኖር መሆኑን ትናገራለች።

**‹‹ ደንበኞቻችን በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ናቸው ፡፡ በዱባይ ፣ በአሜሪካ፣ በፈረንሳይ ፣ በጀርመን እና በሌሎችም ሀገራት የሚገኙ ደንበኞች አሉን ፡፡ የውጭ ሀገር ዜጎች ሆነው ኢትዮጵያ በስራ ላይ ያሉ ሰዎች ወይም ቤተሰቦቻቸውም በእኛ በኩል ስጦታ ይልካሉ ፡፡ ››**

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ግርማ መንግሥቴ**

በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ አምዳችን በአንጋፋው ጋዜጣ በ1960ዎቹ አጋማሽ ለንባብ የበቁ የተለያዩ ዘገባዎችን መርጠናል፡፡ ለማስታወስ የመረጥናቸው ርዕሰ ጉዳዮች በዚያ ዘመን መሠረታዊ የነበሩና ዛሬ ላይ ሆነን ያንን ጊዜ የሚያሳዩን ናቸው፡፡

### የቅድመ ታሪክ አጥኚ ጓድ በ3 ጠ/ግዛቶች ይሰማራል

አዲስ አበባ፤ (ኢ.ዜ.አ.) ከልዩ ልዩ የባህር ማዶ ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ አርኪዎሎጂስቶችና ሳይንቲስቶች የሚገኙበት አንድ የቅድመ ታሪክ አጥኚ ጓድ በሀረርጌ፣ በአሩሲና በሸዋ ጠቅላይ ግዛቶች እየተዘዋወረ የጥናት ስራ በቅርቡ የሚጀምር መሆኑ ትናንት ተገለጠ።

የጥንታዊያን ታሪኮች ቅርስ አስተዳደር የአርኪዎሎጂ መምሪያ በሰጠው መግለጫ ከልዩ ልዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡት ምሁራን የቅድመ ታሪክ ጥናት ለማድረግ አዲስ አበባ መግባታቸውን ገልጦ፤ ጥናቱም ለሶስት ወሮች የሚካሄድ መሆኑን አስረድቷል።

የጥናት ጓዱም "የአፍሪካ ቀንድ ባህላዊ ቅድመ ታሪክ" የተሰኘውን መጽሐፍ በደረሱት በፕሮፌሰር ጄ. ዴሞንድ ክላርክ የሚመራ ሲሆን፣ እኚሁ ምሁር በተለያዩ የአፍሪካ ክፍሎች የሰሩና በርከት ያሉ የጥናት ጽሑፎችን ያዘጋጁ ታዋቂ ሰው እንደ ሆኑ መግለጫው አስረድቷል።

አርኪዎሎጂስቶቹና ሳይንቲስቶቹ የሚመጡት ከካሊፎርኒያ፣ ከኬምብሪጅ፣ በአውስትራሊያ ከሚገኘው ከማክኳሪ ዩኒቨርሲቲዎች ሲሆን፤ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲም ሚስተር ኢስማኤል ሁሴን ከጓዱ ጋር አብረው በጥናቱ ስራ ተካፋዮች እንደሚሆኑ ተገልጧል።

ጥናቱ የሚካሄድባቸው በደቡባዊው የአፋርና የአዋሽ ግዛት፣ በአዋሽ ብሄራዊ ክልል፣ በድሬዳዋና በገዋኔ፤ እንዲሁም በሀረርጌና በአሩሲ መካከል በሚገኘው ኅብታማ ግዛት መሆኑን በመግለጫው አመልክቷል።

ጥናቱ የሚካሄድባቸው እነዚሁ ስፍራዎች የኢትዮጵያን ረባዳ ሸለቆንና ከፍታ ያላቸውን መሬቶች የሚይዙ ቀበሌዎች መሆናቸውንና ጥናቱም በቀበሌዎቹ በቅድመ ታሪክ ለዘመናት ሰዎች ሰፍረውበት የነበረውን ስፍራ ለይቶ ለማወቅ የሚረዳ በመሆኑ በዚያን ጊዜ የኖሩት ሰዎች ምን አይነት ህይወትና የአኗኗር ዘዴ ይመሩ እንደ ነበር ማረጋገጫን ሊሰጥ እንደሚያስችል አረጋግጧል።

ከዚህም በቀር በእነዚሁ ስፍራዎች የሚኖሩት ሰዎች፣ ለምግቦቻቸው ያውሏቸው የነበሩትን እፅዋትና እንስሳት አፅም ፈልጎ ለማግኘት ጥናቱ እንደሚረዳ ከመግለጫው የተገኘው ዜና አመልክቷል።

ከዚህም ሌላ ጥናት ጓዱ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ከጊዜው ጋር ያሳየውን ለውጥ፣ በተለይም ከአደንና እፅዋትን ከመሰብሰብ አንስቶ ለምግብ የሚሆኑ እህሎችን በእርሻ ማብቀል እስከ ተጀመረበት ድረስ ያሉትን ሁሉ ለውጦች ለይቶ ለማወቅ ምርመራና ጥናት እንደሚያካሂዱ ተገልጧል። (ጽሑፉ ይቀጥላል ፨ ፨ ፨)

(አዲስ ዘመን፣ ታህሳስ 26 ቀን 1966 ዓ.ም)

### ብርሀንና ሠላምና ሠራተኞቹ የኅብረት ውል ተፈራረሙ

የብርሀንና ሠላም ማተሚያ ቤት የአሰሪው ወገንና የሠራተኞች ማህበር ለሶስት አመት የሚቆይ የህብረት ስምምነት በትናንትናው እለት በህዝባዊ ኑሮ እድገትና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በተደረገው ሥነሥርአት ተፈራርመዋል።

በህዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር በተደረገው የጋራ ስምምነት መፈራረም ሥነሥርዓት ላይ የአሰሪና የሠ ራተኞች ጉዳይ የቦርድ ሊቀ መንበር ክቡር ፊታውራሪ ደምሴ ተፈራና ሌሎችም ከፍተኛ ባለ ስልጣኖች ተገኝተዋል። ከጥቅምት 1 ቀን ጀምሮ በስራ ላይ የሚውለውን ይህንን ስምምነት የፈረሙት በማተሚያ ቤቱ ስም አቶ አባተ ልመንህ የብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ ሲሆኑ፣ ከሠራተኞቹ ወገን ደግሞ የማተሚያ ቤት ሠራተኞች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ክፍሌ ተስፋጽዮን ናቸው።

ክቡር ፊታውራሪ ደምሴ ተፈራ ሁለቱ ወገኖች ስምምነቱን በተፈራረሙበት ወቅት በተናገሩት ቃል፤ በመካከላችሁ ሶስተኛ ቡድን ሳይገባና አስማሚ ሳያስፈልጋችሁ በመግባባት የህብረት ስምምነቱን እዚህ ደረጃ ስላደረሳችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ካሉ በኋላ፣ ይህ ድርጊት ሌሎች ሊከተሉት የሚገባ መልካም አርአያ ነው በማለት ወደፊትም በመካከላቸው ሊፈጠር የሚችል ውዝግብ ቢኖር እንዳለፈው ጊዜ ሁሉ በቅን መንፈስ በመወያየት ተስማምተው እንዲሰሩ አሳስበዋል።

የብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኞች ማህበር የተቋቋመው በ1959 ዓ/ም ሲሆን፣ ከአሰሪው ጋር የህብረት ስምምነት ሲፈራረም የአሁኑ የመጀመሪያ ጊዜው ነው። በመካከሉ በተፈጠሩት አንዳንድ ምክንያቶች ማህበሩ ከፈረሰ በኋላ ከአንድ አመት በፊት እንደገና የተቋቋመ መሆኑን የማህበሩ ፕሬዚዳንት አስረድተዋል።

ማህበሩ ባዘጋጀው የህብረት ስምምነት ረቂቅ መሰረት፣ በሳምንት ሁለትና ሶስት ቀን በመደራደር ያለ ብዙ ጭቅጭቅ ሁለቱ ወገኖች ስምምነት ላይ ለመድረስ ሁለት ወር ብቻ የፈጀባቸው መሆኑን አቶ ክፍሌ ገልጠዋል። በተጨማሪ ማህበሩ በአሁኑ ጊዜ ሶስት መቶ የሚደርሱ አባል ማህበርተኞች እንዳሉት አስረድተዋል።

(አዲስ ዘመን፣ ታህሳስ 4 ቀን 1966 ዓ.ም)

### አንድ ጥያቄ አለኝ

ስለሺ መኮንን፣ ከጎንደር:-

በጎንደር ከተማ አዲስ ጋዜጣ ተቋቁሟል። በወር አንድ ጊዜ ይታተማል። እንዳይቋረጥ አበርታልን። ጋዜጣውንም አብሬ ልኬልሀለሁ።

*አየሁት። እደግ ተመንደግ የሚያሰኝ ነው። ጋዜጣውን እንዳነበብኩት ይህን ያህል አጥጋቢ ወሬ ባይኖረውም ጀማሪ ነውና አጀማመሩም ቢሆን የሚያስደስት ነው። አንድ ይልቅ ደስ ያላለኝ ነገር አለ። "ጋዜጣው በ10 ሳንቲም ተሸጦ ራሱን እንደሚችል ተስፋ አለን" ይላል። በዚህ አይነት ሁኔታ ማለት እራሱን እናስችላለን በሚል ሁኔታ የተቋቋሞ እንደ ሆነ እድሜው የሚረዝም አይመስለኝም። በየትም አገር ቢሆን በራሱ ሽያጭ ብቻ ራሱን የሚችል ጋዜጣ የለም። ብዙ ማስታወቂያዎች እንዲወጡበት ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ ማስታወቂያ በጎንደር በብዛት የሚገኝ አይመስለኝም። ስለዚህ ጋዜጣውን የጎንደር ማዘጋጃ ቤት ለጋዜጣው ነዋሪ የሆነ በጀት ሊቆርጥለት ይገባል። ገቢም ቢገኝ ለራሱ እየወሰደ ሲሆን ለስራው ማስፋፊያ እየተወለት ቢሄድ መልካም ይመስለኛል። እንዲህ በየጠቅላይ ግዛቱ አንዳንድ ጋዜጦች ብቅ ሲሉ የመሻሻል ምልክት ከመሆኑም ሌላ እጅግ የሚያስደስት ነውና ሌሎቹስ ጠቅላይ ግዛቶች እንዴት ናቸው? በማተሚያ ቤት ማሳበብ መቼም አይቻልም። አሳቡ ካለ አዲስ አበባ እየታተመ ሊደርስ ይችላልና ነው። ጎንደሮች፣ ጋዜጣችሁን ሁሉንም የሚያስንቅ አድርጉት።

ፓውሎስ ኞኞ:-

(አዲስ ዘመን፣ ታህሳስ 6 ቀን 1966 ዓ.ም)

### የአዳጊ አገሮች የሲኒማ በአል አልጀርስ ተጀመረ

አልጀርስ፤ አንድ ሳምንት የሚቆየው የአዳጊ አገሮች የሲኒማ በአል አልጀርስ ከተማ ውስጥ የተጀመረ መሆኑ ተገለጠ። በአሉን በሊቀመንበርነት እንዲመሩ የተመረጡት የአልጄሪያ ፊልም ሰሪ የሆኑት ላሚኒ መርባህ ሲሆኑ፣ የሴኔጋሉ ሴሚባ ኡስሜነረና የኩባንያው ሴኞር ሳንቲያጎ አልቫሬዝ ምክትል ሊቀመንበር ሆነው ተመርጠዋል።

የአዳጊ አገሮች ፊልም ሰሪዎች፣ አቅራቢዎች፤ በዚህ በአል ላይ የተገኙ የፊልም ስራዎቻቸውን የሚመለከቱ ጉዳዮችን እንደሚመረምሩ ታውቋል። ከሚመረምሯቸው ጉዳዮች መካከል ስለ ፊልም ማከፋፈል ችግር ጉዳይ እንደሚነጋገሩ ታውቋል። ብዛታቸው ከፍ ያሉ በአዳጊ አገሮች የተሰሩ ፊልሞች በበአሉ ላይ እንደ ታዩ ታውቋል።

(አዲስ ዘመን፣ ታህሳስ 4 ቀን 1966 ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ




## የሠራተኞች እጥረት ያጋጠማት ጀርመን ተጨማሪ 200 ሺህ የሥራ ቪዛዎችን አጸደቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ከፍተኛ የሠራተኞች እጥረት ያጋጠማት ጀርመን በተለያየ ሙያ ለሰለጠኑ ባለሙያዎች 200 ሺህ የስራ ቪዛ ልትሰጥ መሆኑን አስታውቃለች።

የሠራተኞች ፋላጎትን ለማሟላት የቪዛ አሰጣጥ ስርአቷን ቀለል ባደረገችው ጀርመን ዘንድሮ ይሰጣል የተባለው የሰለጠነ የሰው ሀይል ቪዛ ከባለፈው አመት ጋር ሲነጻጸር በ10 በመቶ ብልጫ ያለው ነው፡፡

በርሊን ባለፈው አመት ከካናዳ የተዋሰችው “ኦፖርቹኒቲ ካርድ” በመባል የሚታወቀው አሰራር ለባለሙያዎች እና ለዩኒቨርሲቲ ምሩቃን ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው እንዲማሩ እና ስራ መፈለግ ቀላል እንዲሆንላቸው አድርጓል። ይህም ሆኖ በሀገሪቱ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ሠራተኞችን የሚፈልጉ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን የሚጠጉ የስራ ዘርፎች ክፍት ሆነው እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

ከአውሮፓ ውጪ የሚገኙ ሙያ ያላቸው ሠራተኞች የሙያ ማረጋገጫ ማቅረብ ሳይጠበቅባቸው ለቪዛ እንዲያመለክቱ ተፈቅዶላቸዋል፡፡ሶስት የጀርመን የመንግሥት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ባወጡት መግለጫ በአመቱ መጨረሻ ከተለያየ የዓለም ክፍል የሚገኙ 200 ሺህ የስራ ቪዛ አመልካቾችን ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

መግለጫው አክሎም አመልካቾች በጀርመን ለመማር እና ለመስራት ሲያመለክቱ ተጨማሪ የሙያ ስልጠናዎች እንደሚሰጣቸው ገልጿል፡፡የአውሮፓ ህብረት ላልሆኑ ሀገራት ተማሪዎች የሚሰጠው ቪዛ በአሁኑ ወቅት በ20 በመቶ ጨምሯል፡፡

የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ናንሲ ፋዘር “ ምስጋና ለኦፖርቹኒቲ ካርድ ይግባውና ባለሙያ ወጣቶች ስልጠናቸውን እና ትምህርታቸውን በጀርመን በቀላሉ ማጠናቀቅ ይችላሉ፤ ልምድ እና አቅም ያላቸው ሰዎች አሁን ተስማሚ ስራ በፍጥነት እና በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ” ብለዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ አናሊና ባርቦክ በበኩላቸው፤ “ጀርመን በየዓመቱ 400ሺህ ብሩህ አእምሮዎች እና ሀገራችንን ጠንካራ የሚያደርጉ ተጨማሪ እጆች ይጎድሏታል፤ ይህ ኢኮኖሚያችንን እንዲያዘግም ምክንያት ሆኗል” ሲሉ ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም ይህን ለመቅረፍ በአውሮፓ እጅግ ዘመናዊ የሆነውን የኢሚግሬሽን ህግ ፈጥነን ተግባራዊ እናደርጋለን ነው ያሉት፡፡

“ኦፖርቹኒቲ ካርድ” (የቪዛ እድል ካርድ) ምንድን ነው?

በርሊን ከካናዳ የወሰደችው የእድል ቪዛ ካርድ ተሞክሮ አንድ ሰው በብቃት፣ በእውቀት እና ልምዱ መሰረት ለቪዛው ብቁ መሆኑን ለመወሰን የሚረዱ ነጥቦች የሚፈተሽበት ነው፡፡

የሙያ ሁኔታዎች ፣ እድሜ፣ የጀርመን እና የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ እንዲሁም ከጀርመን ጋር ቀደም ሲል የነበረ ግንኙነትም ለቪዛው ብቁነት መገምገሚያነት ከተቀመጡ መስፈርቶች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ የሚያመለክቱ ሰዎች በጀርመን በሚቆዩበት ጊዜ በወር አንድ ሺህ ዩሮ የሚጠጋ ገንዘብ በባንክ ሂሳባቸው ውስጥ ሊኖር ይገባል፡፡

ጀርመን ባለፉት አምስት አመታት ወደ 1ነጥብ 6 ሚሊዮን የሚጠጉ ስራዎችን የፈጠረች ሲሆን ከዚህ ውስጥ 89 በመቶ የስራ መደቦች በውጭ ዜጎች የተያዙ መሆናቸው የዶቼቬለ ዘገባ አመልክቷል።

## የሄዝቦላህ የሚዲያ ኃላፊ በቤይሩት በእስራኤል ጥቃት ተገደለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሄዝቦላህ የሚዲያ ኃላፊ መሃመድ አፊፍ እስራኤል በመዲናዋ ቤይሩት በፈጸመችው ጥቃት መገደሉን ታጣቂው ቡድኑ አረጋገጠ።

ሕዝብ በሚበዛበት ራስ አል ናባ በተሰኘው ሰፈር የሚገኘውን የባዝ ፖለቲካ ፓርቲ ዋና መስሪያ ቤት እስራኤል በአየር ጥቃት መምታቷን የሊባኖስ መንግሥታዊ ሚዲያ ዘግቧል። የሀገሪቱ ጥበቃ ሚኒስቴር አራት ሰዎች መሞታቸውን ቢገልጽም የሰለባዎቹን ስም ዝርዝር አልጠቀሰም።

ከሄዝቦላህ ከቀሩት ጥቂት ባለስልጣናት እና ከፓርቲው ፊት አንዱ የሆነው አፊፍ ለመጨረሻ ጊዜ የታየው ቡድኑ መቀመጫውን ባደረገበት በቤይሩት ደቡባዊ አካባቢ ሰኞ እለት ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጠበት ወቅት ነው። ኃላፊው መሞቱ ሪፖርት ከተደረገ ከሰዓታት በኋላ ሄዝቦላህ እሁድ አመሻሹ ላይ መሞቱን አረጋግጧል።



መሃመድ አፊፍ

በጥቃቱ የሊባኖስ ቅርንጫፍ የሆነው የሶሪያ ባዝ ፓርቲ ዋና መስሪያ ቤት አብዛኛው ህንጻው ክፍል ወድሟል። የነፍስ አድን እና የሲቪል መከላከያ አባላት በፍርስራሹ ውስጥ ተቀብረው የነበሩ ሰዎችን ህይወት ለመታደግ ሲሰሩ እንደነበር የሀገሪቱ የዜና አገልግሎት ዘግቧል። የሀገሪቱ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከተገደሉት አራት ሰዎች በተጨማሪ 14 ሰዎች መቁሰላቸውንም አስታውቋል።

የሊባኖስ ባዝ ፓርቲ በሶሪያው ፕሬዚዳንት በሽር አል አሳድ የሚመራው የሶሪያ ባዝ ቅርንጫፍ ፓርቲ እና የረዥም ጊዜ የሄዝቦላ አጋር ነው። በሊባኖስ የሚገኘው ዋና መስሪያ ቤት የሚገኘው በመዲናዋ ቤይሩት በሚገኝ ሕዝብ በከፍተኛ ሁኔታ በሚጨናነቅበት ማዕከላዊ ስፍራ ላይ ነው።

ይህንንም ጥቃት ተከትሎ እስራኤል ከሄዝቦላህ ባለስልጣናት ባለፈ ጥቃቷን እያሰፋች ነው የሚል ስጋት እንዳለ የቢቢሲ የመካለኛው ምስራቅ ዘጋቢ ሊና ሲንጃብ ትናገራለች። ሄዝቦላህ በፓርላማ ተወካዮች እና በመንግሥታዊ መዋቅሮች ውስጥ ሚኒስትሮች ያሉት የፖለቲካ ፓርቲ ነው።

“ይህ ጥቃት ሁኔታውን የሚያባብሱ ወይም መፍትሄ የመሻት ምልክቶች እንደሌሉ ለበርካቶች የማንቂያ ደወል ነው። ይልቁንም የበለጠ እየተባባሰ እና እስራኤል በሊባኖስ እያደረገችው ያለው ኢላማ እየሰፋ መምጣቱን ያሳያል” ብላለች።

ህዳር 8 ቀን 2017 ዓ.ም በማዕከላዊ ቤይሩት በማር ኤሊያስ ጎዳና ላይ በተፈጸመ ሌላ ጥቃት ሁለት ሰዎች ሲሞቱ 13 ተጨማሪ ሰዎች መቁሰላቸውን የሊባኖስ ጤና ሚኒስቴር አክሏል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ዘመን
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንና ፌስቡክ ገጾቻችን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ማክሰኞ
ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ- በማራቶን ከዋክብቱ አንደበት

ዓስማየሁ ግዛው

ሃያ አራት ዓመታትን ያስቆጠረው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የዓለም አትሌቲክስ የ‹‹ሌብል›› ደረጃና እውቅና በሰጠው ማግስት ከትናንት በስቲያ 50 ሺ ሰዎችን ያሳተፈ ትልቅ ውድድር አካሂዶ በስኬት ማጠናቀቅ ችሏል። ይህም ለትልቁ የአፍሪካ የጎዳና ላይ ውድድር ድርብ-ድል ከማጎናጸፉ በላይ ውጤታማና ተተኪ አትሌቶችን የማፍራት የሚያደርገውን ጥረት የሚያጠናክርና ትልቅ አቅም እንደሚሆነው ታምኖበታል። ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ እድገት የሚያበረክተው አስተዋጽዖና ከትልቅ የዓለማችን የጎዳና ላይ ውድድሮች አንዱ እንዲሆን እንዳስቻለውም የወቅቱ የማራቶን ከዋክብት አትሌቶች መስክረውለታል።

በዘንድሮው ውድድር በክብር እንግድነት የተገኙት ኢትዮጵያዊው የወቅቱ የኦሊምፒክ ማራቶን አሸናፊ አትሌት ታምራት ቶላና ከወር በፊት የሴቶችን የማራቶን የዓለም ክብረወሰን ያሻሻለችው ኬንያዊት አትሌት ሩት ቼፕንጌቲች የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያን ታላቅነት የመሰከሩ አትሌቶች ናቸው። ሁለቱ የወቅቱ የማራቶን ኮከቦች ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ‹‹ትልቅ ደረጃ ላይ መቀመጥ የሚችል፣ ወጣትና እውቅ አትሌቶችን የሚያፈራ ነው›› ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

የ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ማራቶን አሸናፊው አትሌት ታምራት ቶላ፣ በ2008 ዓ.ም በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ውድድር ላይ የተሳተፈ አትሌት ነበር። ውድድሩ በአሁኑ ወቅት ማደጉን እና የተሻለ ደረጃ ላይ መድረሱን የተናገረው ታምራት፣ በመድረኩ የሚያሸንፉ አትሌቶች በኦሊምፒክና ዓለም



የማራቶን ኦሊምፒክ ቻምፒዮኑ ታምራት ቶላና የማራቶን ባለክብረወሰኗ ሩት ቼፕንጌቲች የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የክብር እንግዳ ነበሩ፣

ቻምፒዮና ሀገርን የሚወክሉ በመሆኑ ትልቅ ውድድር እንደሚያሰኘው ጠቁሟል። ‹‹በዓለም አትሌቲክስ በቅርቡ የጎዳና ላይ ሌብል (Road label race) ደረጃ ማግኘቱ ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ትልቅ ጥቅም ይኖረዋል›› በማለትም የዓመቱ ከቤት ውጪ ውድድሮች ኮከብ አትሌቶች እጩ ተናግሯል።

እንደ ታምራት አስተያየት፣ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ለዓለም አቀፍ ውድድሮች የሚያሳትፋቸውን ሰዓት ለማሟላት ውጪ ሀገር ሄደው የሚወዳደሩበትን ሁኔታ የማስቀረት አቅም አለው። ከተለያዩ ዓለማት ትልልቅ አትሌቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የሚሳተፉበትን እድልም ይፈጥራል። ይህም ለኢትዮጵያውያን አትሌቶች አቋማቸውን በሀገራቸው ለመፈተሽና በዓለም አቀፍ ውድድሮች ለመወዳደር በር ይከፍታል። ሀገርን ወክለው ተፎካካሪና ሜዳሊያ የሚያስመዘግቡ አትሌቶችን ለማፍራትም ጥሩ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ብሏል።

ታላቁ ሩጫ የስኬታማ የአትሌቲክስ ጉዞው መነሻ መሆኑን የሚያስታውሰው አትሌት ታምራት፣ መጀመሪያ በታላቁ ሩጫ አሸንፎ በኦሊምፒክና ዓለም ቻምፒዮና ሀገሩን መወከል እንደቻለ ይናገራል። የሴቶች የዓለም ማራቶን ክብረወሰንን ያሻሻለችው አትሌትና ሌሎች ታላላቅ አትሌቶችም በክብር እንግድነት እንዲሁም ለተሳትፎ መምጣታቸው ወጣትና ጥሩ አትሌቶችን ለማፍራት ትልቅ የሞራል ስንቅ እንደሚሆን ጠቅሷል።

ኬንያዊቷ የወቅቱ የማራቶን ክብረወሰን ባለቤት ሩት ቼፕንጌቲች ለመጀመርያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የዘንድሮው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ውድድር የክብር እንግዳ ሆናለች። አትሌቷ ከልጅነቷ ጀምሮ ትልልቅ ኢትዮጵያውያንና ኬንያውያን አትሌቶች ልምምድ ሲሰሩና ውድድሮችን ሲያደርጉ እያየች ማደጓን አሁን ላይ ክብረወሰን እንድታሻሽል እንዳነሳሳት ተናግራለች። ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አፍሪካ ውስጥ ከሚካሄዱት ውድድሮች ትልቅ ደረጃ የሚሰጠውና ቀዳሚው እንደሆነም ገልጻለች። ሩት አጠቃላይ ውድድሩና የተሳተፊውን ሕዝብ ብዛት እንዳስደነቃት እንዲሁም ተፎካካሪ አትሌቶችን መመልከቷን ጠቁማለች። ውድድሩ የተቀናጀ፣ ወጥነት ያለው፣ መስተንግዶውም ጥሩ በመሆኑ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ትልልቅ አትሌቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንዲወዳደሩም መልዕክቷን አስተላልፋለች።

ባለፈው የቺካጎ ማራቶን የዓለም የማራቶን ክብረወሰንን በእጇ በማስገባቷ ደስተኛ እንደሆነችና ሕልሟ እውን እንዳደረገችም ተናግራለች። በኢትዮጵያውያን እና ኬንያውያን አትሌቶች መካካል የሚደረገው ፉክክር አስደሳች እንደሆነና ታዳጊ አትሌቶችን ለማፍራት እንደሚረዳም ጠቅሳለች። ወጣት አትሌቶች እንደ አትሌት ኃይሌ፣ ጥሩነሽ፣ መሠረት ውጤታማ ለመሆን ጥሩ ባህሪን ተላብሰው ጠንክረውና በርትተው መስራት ይጠበቅባቸዋልም ብላለች።

አትሌት ሩት ቼፕንጌቲች የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የክብር እንግዳ ስለመሆኗ እና ታላቁ ሩጫ እያሳያ ስላለው እድገት አስመልክቶ ዘገባ የሰራው የኬኒያው ኔሽን ጋዜጣ፤ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በዓለም ካሉ ትልልቅ የሩጫ ውድድር ፌስቲቫሎች ለመመደብ በትክከለኛው ጎዳና ላይ ይገኛል ብሏል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ